

ባሕታዊ መፍቀሬ ስብእ የተለያዩ ዘሮችን ያለሙለት የቆብ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን፡

# ትንሣኤ



ባሕታዊ መፍቀሬ ስብእና ጓደኞቻቸው ገጠሪቱ ኢትዮጵያን አረንጓዴ ለማልበስ በዚህ ሁኔታ የተ ስለፉት ከ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ጀምረው ነው፡

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም

ቁጥር 42

መጋቢት ፲፱፻፸፫ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

''ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረ ጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ ''ትንሣኤ'' ተብሎ ተሰይሟል ።

አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ
ም/አዘጋጅ ሪደ አስረስ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

# ማውጫ

አርእስት ገጽ

ደብዳቤዎች ............ ፩
የመምጣትህ ምልክቱ ምንድን ነው ? ............ ፪
እንዲህ ነው ባሕታዊ ! ............ ፬
ክርስቲያን ሴቶች እንዴት ይኖራሉ ? ............ ፯
ጾም መጾም ከምንና ከምን ነው ? ............ ፯
ዕውነተኛ ነፃነት የተጋደሎ ውጤት ............ ፰
ቤተ ሰብእ ............ ፱
የአቡነ ጴጥሮስ ሕፃናት ማሳደጊያ ደሴ ............ ፲
ምን እንርዳዎ ? ............ ፲፪
ምሥጢረ ንስሐ ............ ፲፫
ይህን ያውቁ ኖሯል ? ............ ፲፭
ልማት በቤተ ክርስቲያን ............ ፲፮
ሊቃውንቶቻችን ............ ፲፰
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች ውድድር ............ ፳

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

1ኛ አንድ ሰው በተወለደ በስንት ዓመቱ ዲቁና ሊቀበል ይችላል ፣ ዲቁናስ ከተቀበለ በኋላ እስከ ስንት ዓመት ሊቀድስ ይችላል ?

**2ኛ/ ዲያቆን ክህነት ከመቀበሉ በፊት ምን ምን ማሟላት አለበት ?**

**3ኛ/ ዲያቆን ሚስት ማግባት የሚችለው በስንት ዓመቱ ነው ?**

4ኛ መጽሐፍም ሆነ መጽሔትና ጋዜጣ የማንበብ ፍላጐት አለኝ አነብባለሁም ግን በአእምሮዬ አይያዝልኝም ፡ እንዴት አድርጌ በአነብ በአእምሮዬ መቅረጽ እችላለሁ ?

**ያልተማረ ይማር የተማረ ያስተምር**
**የማይሠራ አይብላ**
**ዲያቆን ጥላሁን ገብሬ**
አቃቂ በሰቃ መንበረ ሕይወት መድኃኔ ዓለም

**● ዲያቆን ጥላሁን ገብሬ ጥያቄህን ተመተመልክተነዋል ፣ 1ኛው ጥያቄህ ዲያቆን መሾም የሚገባው 25 ዓመት ሲሆነው ነው ። ዲያቆን 25 ዓመት ሳይሆነው አስቀድሞ መሾም እንደማይገባው** በፍትሕ መንፈሳዊ በ7ኛው አንቀጽ **በቁ . 242 ላይ ተወስኖአል ። ዲቁና ከተቀበለ በኋላም** መላ ሕይወቱን ማገልገል ይቻላል ።

2ኛ/ **ዲያቆን ክህነት ከመቀበሉ በፊት የአንዲት ሴት ባል ማለት በሕጋዊ ጋብቻ የተወሰነ ቤተሰቦቹን በሚገባ የሚያስተዳድር ለችግረኞች የሚያዝን ፊ**ጥኖ የማይቆጣ የማይዋሽ ፊት አይቶ የማያዳላ ሌሎችን የማያሳዝን አብዝቶ የማይጠጣና የማይሰክር ምሥጢራትን ለመመራመር ሰነፍ ያደለ መሆን እንዳለበት ለአንደኛው ጥያቄ መልስ በጠቀስነው አንቀጽ በቁ.240 ላይ ተገልጦአል ።

3ኛ ለዲያቆንም ሆነ ለምእመን የተፈቀደው የጋብቻ እድሜ ከ18 ወይም ከ20 ዓመት በላይ ነው ስለዚህ ከ18 ዓመት በላይ በወደደውና በተሟላለት ጊዜ ማግባት ይችላል ።

4ኛ/ የምታነበውን በአእምሮህ መቅረጽ እንድትችል በመጀመሪያ አንድ ጊዜ አንብበህ ጠቅላላ ሐሳቡን ለመረዳት ሞክር ፣ ሁለተኛ የእያንዳንዱን አንቀጽ ሐሳብ ለማወቅ በጥንቃቄ አንብበው ሦስተኛ ቃላት በቃላት ሐረግ በሐረግ እያነበብህ የቃላቱንና የሐረጐቹን ሐሳብ ተረዳ ፣ በዚህ መንገድ ከ 1-3 ጊዜ መላልሰህ ከአነበብህ በአእምሮህ መቅረጽና ማስተዋል ትችላለህ ።

* * *

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከሁሉ አስቀድሜ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰላም ለሁላችን ይሁን እላለሁ የትንሣኤ መጽሔት ማህበርተኛ ሆኜ መመልከቱን ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ በመጽሔቱ ብዙ ትምህርቶች እያገኘሁ የተከታታዩ ወራት መጽሔት በፖስታ እስኪደርሰኝ ድረስ በጉጉት እጠባበቃለሁ አሁን ልጠይቅ የተነሣሁበት በድርሣን ሰንበት ምዕራፍ 25፣ቁ.5 ላይ ቅዱስ ጳውሎስ የጾመም ለእግዚአብሔር ጾም የበላም ለእግዚአብሔር በላ ይልና ባለፀጋ ግን መጾሙ ገንዘቡ እንዲጠበቅለት ነው እንጂ እግዚአብሔርን ደስ አሰኛለሁ ጥቅም አገኝበታለሁ ብሎ አይደለም ይላል የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሲያስተምሩን ማንኛውም ክርስቲያን ለተወሰነ ጊዜ ከሥጋና ከቅቤ ይኸን ከመሣሰሉት ነገሮች ተከልክሎ በጾምና በጸሎት ተወስኖ ፈጣሪውን ከለመነ ከሠራው ኃጢአት ደህንነትን እንደሚያገኝ ያስረዱናል ። ስለባለፀጋ ጾሞ ገንዘቡን ለመቆጠብ ነው እንጂ እግዚአብሔርን ደስ አሰኛለሁ ጥቅም አገኝበታለሁ ብሎ አይደለም የሚለው ቃል በመንፈሳዊ መጽሐፍ ታትሞ ወጥቶ ትምህርት ሲሰጥበት ባለፀጋ ተለይቶ ሊታይ የቻለበት እንዴት እንደሆነ ተብራርቶ በዚሁ ትንሣኤ መጽሔት ቢገለጽልኝ ጠቃሚ ነው እላለሁ ።

ባላምበራስ በቀለ ደንበለው
አርሲ ኩፈሌ

ባላንምባራስ በቀለ ደንበለው የመጽሔታችን ተከታታይ በመሆንዎ እናመሰግናለን ያቀረቡትም ጥያቄ መልስ ሊሰጥበት የሚገባ ነው ።

በድርሳነ ሰንበት የጾመ ለእግዚአብሔር ጾመ የበላም ለእግዚአብሔር በላ የሚለውን የሐዋርያውን የጳውሎስን ቃል በማዛመድ ባለጸጋ የሚጾመው ገንዘቡ እንዲጠበቅለት እንጂ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት አይደለም የሚል ቃል ተጽፏል ይህ እንዴት ነው? በማለት ያቀረቡት ጥያቄ እርስዎ እንዳሉት ተጽፎ ከተገኘ ስሕተት ስለሆነ በእኛ በክርስቲያኖች ዘንድ ቦታ የለውም ።

ጾም የሚሰጠው ዋጋ ለሀብታምና ለድሀ ሊከፈል አይችልም ባለጸጋም ሆነ ድኃ የሚጾመው ለአንድ እግዚአብሔር ስለሆነ ሁለቱም እንደሚገባ ከጾሙ ከእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋቸውን ይቀበላሉ እንጂ ባለጸጋው ለሀብቱ መጠበቂያ ድሃ ለራሱ መጽደቂያ ይጹም የሚል በቤተ ክርስቲያን የለም ።ምን አልባት በድርሳን ሰንበት የተጻፈው እየጾመ ምጽዋት የማይሰጥ ለተቸገሩት የማይራራ ባለጸጋ ገንዘቡን ለመቆጠብ ያህል ይጾማል እንጂ ጾሙ ዋጋ የለውም ማለቱ ከሆነ ልክ ይሆናል ምክንያቱምእውነተኛ ጾም ማለት በጾም ምክንያት የተወውን ምሳ ወይም ቁርስ ለችግረኞች መለገስ ነውና ። ስለዚህም የጾም አላማ ለተራቆቱ ልብስ ፣ ለተራቡ ምግብ ማካፈል እንደሆነ በትን.ኢሳ 58 ውስጥ ተገልጦአል ። ይህም እንደየችሎታው ጻዋሚዎችን ሁሉ እንጂ ባለጸጎችን ብቻ የሚመለከት አይደለም ።

ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# "የመምጣትህ ምልክቱ ምንድነው?"

ማቴ . 24 :3

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት የእግዚአብሔር ወልድ ወደ ዓለም መምጣት የሚነገርባቸው ጊዜያት አሉ ።እነ
ርሱም 1ኛ ከበዓለ ልደት በፊት " ስብከት ብርሃንና ኖላዊ" በመባል የሚታወቁት ሦስት ሳምንታት ናቸው ።
እነዚህም ሳምንታት በመተላለፉ ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይቶ የክብር ስፍራውን በማጣት ተዋርዶ የነበረው
ን ሰው ከፈጣሪው ጋር ለማስታረቅ ወደቦታው ለመመለስ እግዚአብሔር ወልድ ወደ ዓለም መጥቶ ሰው እንደሚ
ሆንና በሰዎች ባሕርይ እንደሚገለጥ አስቀድሞ ቅዱሳን ነቢያት የተናገሩትን ትንቢት የመሰሉትን ምሳሌ ያዩትን ኅ
ብረ አምሳል የምናስታውስባቸው የምንማርባቸውና የምናስተምርባቸው ሲሆኑ ፣ ከልደት እስከ ድራረ ጾም ያሉት
ሳምንታት ደግሞ" እግዚአብሔር ወልድ በሰው ልጆች ፍቅር ተገድዶ ወደ ዓለም መጣ ከሰማየ ሰማያት ወረደ ያለዘር
አ ብእሲ ከድንግል ማርያም ነፍስና ሥጋን ተዋህዶ ተወለደ" በማለት ቀዳማዊ ምጽአቱን የምንሰብክባቸው ሳምንታ
ት ናቸው ።

እግዚአብሔር ወልድ ዳግመኛ ወደ ዓለም እንደሚመጣና በሰዎች ፊት እንደ ሚገለጥ በቅዱሳት መጻሕፍት ተገልጦ
አል፣ ግን ዘመኑና ጊዜው መቼ እንደሆነ ከራሱ ከእግዚአብሔር በቀር ማንም የሚያውቅ የለም ። ማቴ. 24፥36 ጊዜውና ዘ
መኑ ባይታወቅም ሰዎች በማያስቡትና በማይጠረጥሩት ዕለት እንደሚገለጥ ክርስቲያኖች ሁሉ ያምናሉ።

ስለዳግም ምጽአቱ በብሉይና በሐዲስ ኪዳን የተነገሩትን ምልክቶች የምናስታውስባቸውና የምንመረምርባቸው ሳም
ንታት 1ኛ በዓቢይ ጾም አምስተኛውና ደብረ ዘይት በመባል የሚተወቀው ሳምንት 2ኛ አምስቱ ዕለታት ጳጉሜ 3ኛ ከወ
ርኃ ጽጌ በኋላ በሚሆነው ዘመነ አስተምሮ የመጨረሻው እሁድ ሲሆን አንዳንድ ዓመት ይህ እሁድ የማያገኝበት
ጊዜ አለ ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ዘይት ተራራ ተቀምጦ ሳለ ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው"ዳግመኛ የመምጣትህ
ምልክቱ ምንድንነው? " ሲሉ ጠየቁት ማቴ 24 ፡ 3 እርሱም « ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ ብዙዎች እኔ ክርስቶ
ስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና ብዙዎችንም ያስታሉ» ከአለበኋላ የጦርነት ወሬ በየጊዜው እንደሚሰማ ሕዝብ በሕዝብ
መንግሥታት በመንግሥታት ላይ እንደሚነሡና ረኃብ፣ቸነፈርና የምድር መናወጥም በየስፍራው እንደሚሆን በዚያ
ም ጊዜ በብዙ ሰዎች ዘንድ ፍቅር እንደሚቀዘቅዝ ግን ወንጌል በዓለም ሁሉ እንደሚሰበክ ነገራቸው ማቴ 24፡3-14 ።

ሐዋርያዊ ቅዱስ ጳውሎስም ክርስቶስ ዳግመኛ የሚመጣበት ዘመን ሲቃረብ ሰዎች ራሳቸውን ወዳድ ፣ ገንዘብ ወዳጆ
ች ... የማይታዘዙና የማያመሰግኑ ፍቅርና ቅድስና የሌ
የማይሉ፣ ትምክህተኞች፣ ትዕቢተኞችና ተሳዳቢዎች ለወላጆቻቸው የማይታዘዙና የማያመሰግኑ ፍቅርና ቅድስና የሌ
ላቸው ዕርቅን የማይሰሙ ሐሜተኞች ራሳቸውን የማይገዙ ጨካኞች ከዳተኞችና ችኩሎች እንደሚሆኑ ለደቀ መዝ
ሙሩ ለጢሞቴዎስ ሁለተኛ ጊዜ በጻፈው መልእክቱ ገልጦአል። 2ኛ ጢሞ. 3፡ 2 - 6።

ይሁን እንጂ የኋለኛው አመጣጡ ከቀደመው አመጣጡ የተለየ ነው። የቀደመው አመጣጡ በትሕትና በአርአያ ገብር
ነበር የኋላው አመጣጡ ግን በግርማ መለኮት (በጌትነት) ነው የቀደመው አመጣጡ ለነፃ ነበር የኋላው አመጣጡ ግን
ዋጋ ለመስጠት ነው ማለት መልካምለሠራ በቃሉ ለመአነና በሕጉ ለጸና ዋጋ መልካም ላላደረገ በቃሉ ላላመነና በሕጉ
ላልጸና ፍዳ ለመክፈል ነው። የቀደመው አመጣጡ ኃጥአንን በንስሐ ለመጥራት የጠፉትን ለመፈለግ የተጎዱትን ለመር
ዳት የተበተኑትን ለመሰብሰብና ለማዳን ነበር ይህንንም « ዓለምን ላድን እንጂ በዓለም ልፈርድ አልመጣሁም » እያለ
ለሠላሳ ሦስት ዓመታት ያህል በሰዎች በካከል ከኖረና ወንጌልን ከአስተማረ በኋላ በራሱ መሥዋዕትነት በሰውና በእ



ግዚአብሔር መካከል የነበረውን የበደል ግድግዳ አስወግዶ አዳምን ከነልጆቹ ወደ ቀድሞ ቦታው መልሶ አረገ።
የማዳን ሥራውን ፈጽሞ በዓረገም ጊዜ « እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ ትሆኑ ዘንድ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም
እወስዳችኋለሁ » በማለት ሁለተኛ የሚመጣው ለሰዎች በሥራቸው መጠን የተዘጋጀላቸውን ቦታ በፍርድ ለማስረከብ
መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል። ዮሐ 14፡ 3።

የቀድሞው ምጽአቱ «በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቀ ዕለት አትወለድ እም ወለተ ወለትከ ወእትቤዘወከ፣ በአምስት ቀን
ተኩል (በአምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን) ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ » ተብሎ በመጽሐፈ ቀቀሌምንጦ
ስ የተወሰነ የዘመን ቁጥር ስለነበረ የአዳም ልጆች ያንን ቀን በተስፋ ይጠባበቁ ነበር ያም ቀን በደረሰ ጊዜ የተነገረ
ው ተስፋ ተፈጸመ ገላ 4፥4 ሁለተኛ የሚመጣበት ጊዜ ግን አይታወቅም ቅዱስ መጽሐፍም ስለዚያች ዕለትና ሰዓት
ማንም አያውቅም ግን ሰዎች በማያውቁትና በማይጠረጥሩት ሰዓት ድንገት ስለሚደርስ ነቅታችሁና ተጠንቃችሁ
ኑሩ ከማለትና በኖኅ ዘመን የነበሩ ሰዎች በመብልና በመጠጥ ተዘልለው በኃጢአት እንዳሉ የጥፋት ውሃ መጥቶ ሁ
ሉን እስከወሰደ ድረስ እንዳላወቁ የሰው ልጅ (የክርስቶስ) መምጣት እንዲሁ ይሆናል ከማለት በቀር ሌላ ምልክት
አይሰጥም ማቴ. 24፡36-39 ።

ስለዚህ ለሰው ልጆች ሁልጊዜ ተዘጋጅቶ መኖር ያስፈልጋል ለተዘጋጁ ክርስቲያኖች ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀ
ዘላለማዊ የሆነ የክብር ቦታ አላቸው ። ቀኑ ሲደርስ ወደዚያ የዕረፍትና የክብር ቦታ ለመግባት ነቅቶና ተዘጋጅቶ መጠ
በቅ ነው ። ክርስቶስ ከተናገራቸው ምልክቶች እንደ ጦርነት እንደ መሬት መንቀጥቀጥ የመሳሰሉት በመሰማት ላይ
ናቸው ። " ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ አትደንግጡ ዳሩ ግን መ
ጨረሻው ገና ነው ።" ማቴ 24፥6 በማለት ራሱ ክርስቶስ ስለአስተማረን በምንሰማው ወሬ በምናየው ድርጊት
መደንገጥ መፍራት የለብንም ከፍርሃትና ከድንጋጤ የተነሣ ሥራ ፈቶች ልን ሆን አይገባንም ። ግን በመልካም ሥራ
ልንተጋ ከኑሮአችንና ሥራችን ልንጠነቀቅ በአላማችንና በእምነታችን እስከ መጨረሻው ልንጸና ይገባናል ። " እስከ
መጨረሻው የሚጸና እርሱ ይድናል" ተብሎ ተጽፎአልና ።



www.ethiopianorthodox.org

# እንዲህ ነው ባሕታዊ !

በሸዋ ክፍለ ሀገር በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ የተወለዱ የ43 ዓመት ሰው ና ቸው አላማቸው ምናኔ ነው ። ባሕታ ዊ መፍዋሬ ሰብብ ይባላሉ የመፍቀሬ ሰብእ ብሕትውና እንደ አንዳንድ አስ መሳይ ባሕታውያን በማታለልና በል መና የተመሠረተ አይደለም ባሕታዊ መፍቀሬ ሰብእ ወንጌልን በማስተማር አብያተ ክርስቲያናትን በማሳደስና በየ አብያተ ክርስቲያናቱ አካባቢ አትክል ት በመትከል ደን በማልማት ከፍተኛ ውጤት ያሳዩና ሥርቶ መኖርን ከወንጌ ል ትምህርት ጋር የሚያስተምሩ ባሕታ ዊ ናቸው ።

ባሕታዊ መፍቀሬ ሰብእ በሥልጣነ ክህነት ያላቸው መዓርግ ዲቁና ነው ፤ ቅስና ቁምስና ለምን አልተቀበሉም? ለ ሚለው ጥያቄ ባሕታዊው የሚሰጡት መልስ "ከሹመት ለመራቅ ነው" የሚ

ል ነው ፤ እንደሚሉትም በ1971 ዓ.ም የጳጳሳት ምርጫ ሲደረግ ለውድድር እን ዲቀርቡ ታጭተው ነበረ ፤ ነገር ግን እ ርሳቸው "ያመነኮሰኝና ያቀሰሰኝ ማን ነው?" በማለት ሹመት የማይፈልጉ መ ሆናቸውን ገልጠው ከውድድሩ ሳይገቡ በመቅረታቸው ከመሾም ድነዋል ።

ባሕታዊ መፍቀሬ ሰብእ በልዩ ልዩ ዛፎች ከአለሙአቸው ቦታዎች ጥቂቶ ቹን ተመልክተናል ባለፈው ታኅሣሥ ወር 73 ዓ.ም. በላሊበላ ተገኝተን በሥ ራ ላይ እንዳሉ አነጋግረናቸዋል ።

የ ባሕታዊ መፍቀሬ ሰብእ በላሊበላ ያለሙትን የዛፍ ተከላ ሥራ ለመጀመር ያሳሰባቸው ምን እንደሆነ ጠይቀናቸው ነበር ፤ ታዲያ ባሕታዊው ይህን ቦታ በ ልዩ ልዩ የዛፍ ተክል እንዳለማው ያነ ሣሣኝ የላሊበላ ታቦታት በየዓመቱ የ

ጥምቀትን በዓል ለማክበር ወንዝ ሲወ ርዱ የሚያደርጉት ረጅምና አድካሚ ጉዞ ነው" ይላሉ ።

ቀደም ሲል የላሊበላ ገዳማት የጥም ቀትን በዓል የሚያከብሩት በግምት ከ 5-6 ኪሎ ሜትር ርቀት ተጉዘው ነበር አሁን ግን ከአብያተ ክርሳቲያናቱ አን ድ ኪሎ ሜትር ተኩል ያህል በሚሆን ወና ባሕታዊ መፍቀሬ ሰብእ ቅጥር ቀ ጥረው ዛፍ ተክለው ባዘጋጁት ቦታ ነ ው ። ባሕታዊ መፍቀሬ ሰብእ ይህን የ ታቦት ማደሪያ ቦታ ለማዘጋጀት ሲያስ ቡ የነበረባቸው ችግር ቦታውን ለታቦ

ት ማደሪያ እንዲሆን በጊዜው ይጠቀ ሙበት ከነበሩት ግለሰቦች የማስፈቀዱ ጉዳይ ነበር ። ሆኖም ባሕታዊው ገዳማ ቱን በማስተባበር ገዳማቱ ገንዘብ አዋ ጥተው በብር 3300 ሦስት ሺ ሦስት



ባሕታዊ መፍቀሬ ሰብእ ስለ ታቦት ማደሪያውና ስለ ሥራቸው ከንውን መግለጫ ሲሰጡ ።



መቶ ብር ያስገዛሉ ፤ ይህ የተደረገው በ 1964 ዓ'ም. ነው ።

ከዚህ በኋላ ባሕታዊ መፍቀሬ ሰብእ ቅጥር መቅጠር ዛፍ መትከል ይጀምራ ሉ አካባቢው በድርቅ የተጐዳ በመሆ ኑ በክረምትም ሆነ በበጋ ለሚተከሉት ዛፎች በቂ የዝናም ውሃ አይገኝም በ አውራጃው ከሚገኘው ከተገዚ ወንዝ ም የተሳበ የቧንቧ ውሃ የለም የተከዚን ም ውሃ በቦይ ማስገባት አልተቻለም አማራጩ የውሃ መቅጃ ሸራና የጋማ ከብት ገዝቶ ብዙ ኪሎ ሜትር በመጓ ዝ ውሃ እየቀዱ በባልዲ ማጠጣት ነ ው ። ባሕታዊ መፍቀሬ ሰብእ ይህን ሥራ በጀመሩ ጊዜ ውሃ ከወንዝ በሸ ራ በመቅዳት ይረዳቸው ዘንድ የገዙ ትን የጋማ ከብት አርጋው ላሊበላ ብ ለው ሰይመውታል ።



ባሕታዊ መፍቀሬ ሰብእ ከጓደኞቻቸው ጋር በሥራ ላይ እንዳሉ ።

ባሕታዊ መፍቀሬና አርጋው ላሊበ ላ መልካም የሥራ ውጤት በአሳዩ ጊ ዜ የላሊበላ ገዳማት ሦስት መነኮሳት ረ ዳት መድበውላቸው አሁን የታቦት ማ ደሪያውን ቅጥር በመቅጠር ዛፍ በመት

ከልና የተተከሉትን ዛፎች ውሃ በማጠ ጣት የሚንከባከቡት ከባሕታዊ መፍቀ ሬ ጋር አራት መነኮሳትና አርጋው ላሊ በላ ናቸው ። እስከ አሁን ድረስ የተተከሉትና የጸደቁት ዛፎች ከ6000-8000 (ከስድስት እስከ ስምንት ሺህ ይ ሆናሉ ። የዛፎቹም አይነት ወይራ ፣ ጥ ድ ፣ ወርካ ፣ ሸንት ፣ ጀባ ፣ ችባሐ ፣ ክት ክታ ፣ ደደሆ ቁንዶ በርበሬ ፣ ባምባ ፣ሾ ላና የተለያዩ የአበባ አይነቶች ናቸው የዛፉ ተከላ ወደፊትም እንደሚቀጥል ባሕታዊ መፍቀሬ ሰብእ አስረድተዋል ባሕታዊ መፍቀሬ ለታቦታቱ ማደሪያ በየጊዜው ድንኳን ከመሸከም የሚ ያድን ቀዋሚ ሕንፃ ለማሠራት በዝግጅ ት ላይ ናቸው ፤ በርከት ያሉ የተጠረቡ ድንጊያዎችን አቅርበዋል ፤ ጥምቀተ ባ ሕርም (መዋኛ) ለማሠራት ጉድጓድ አ

ስቆፍረው ፤ ደንጊያ አቅርበው አሸዋና ሲሚንቶ በመፈለግ ላይ ናቸው ። ጥም ቀተ ባሕሩ (መዋኛው) የሚሠራው ጐን ደር ከተማ በሚገኘው ጥምቀተ ባሕር አምሳል ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ እንደ

ተጠመቀ የሚያሳይ እንደሚሆን ባሕ ታዊ መፍቀሬ ያስረዳሉ ።

የባሕታዊ መፍቀሬ የልማት ሥራ በላሊበላ ብቻ የተወሰነ አይደለም እን ዲሁም ከቁልቋልና ከቅንጭብ በቀር ሌላ ዛፍ በማይታይበት በራያና ቆቦ አ ውራጃ በቆቦ መድኃኔዓለም ቤተ ክር ስቲያን በሺህ የሚቆጠሩ ዛፎችን አት ክለው አጽድቀዋል ፤ ያን የተመለከቱ የወረዳው ባለሥልጣኖችም በቤተ ክር ስቲያኑ ዙሪያ ያለውን ቦታ ሁሉ ዛፍ እ ንዲተክሉበትና እንዲያለሙት የፈቀዱ ላቸው መሆኑን ባሕታዊ መፍቀሬ አ ልሰወሩም ። እንዲሁም በአምሳል አው ራጃ በግሸንና በሐይቅ ዛፎችን በመት ከልና ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችን በማ ከናወን ረገድ የታወቁት ባሕታዊ መፍ ቀሬ ሰብእ ለሌሎች ባሕታውያን ምሳ

ሌ ሆነው ሊጠቀሱ የሚገባቸው ዕው ነተኛ ባሕታዊ ናቸው ።

ተክል ተክሎ ለማጽደቅ ዘር ዘርቶ

ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

## ክርስቲያን ሴቶች እንዴት ይኖራሉ?

በህዳር ወር በወጣው ትንሣኤ መጽሔት ቁጥር 38 ላይ ከእንዲት ወይዘሪት ስለ ክርስቲያን ሴቶች አኗኗር እንዴት መሆን አለበት፣ በማለት ያቀረቡትን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ተነስተን ያላገቡ ክርስቲያን ሴቶች አኗኗር እንዴት እንደሆነ መግለጻችን የሚታወስ ነው ።

በአሁኑ ጽሑፋችን ደግሞ በትዳር ላይ ያሉት ክርስቲያን ሴቶች አኗኗር እንዴት መሆን እንዳለበት ልመግለጽ እንሞክራለን ።

መጽሐፍ ቅዱስ "አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል ቢወድቁ አንዱ ሁለተኛውን ያነሳዋልና ይላል መክብብ 4፡9-10

ይህም በክርስቲያናዊ ጋብቻ ከተጋቡበት ዕለት ጀምሮ አንድ አካል ስለሆኑ በመተማመን ፣ በፍቅርና በሰላም አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ ተባብለው በመተሳሰብ መኖር እንዳለባቸው ይገልጻል ።

ስለጋብቻ ጉዳይ አስመልክቶ አንድ የጀርመን ጸሐፊ ሲጽፍ "ለራሳቸው ብቻ መደሰት የሚፈልጉ ሰዎች ማግባት አይገባቸውም ምክንያቱም በጋብቻ አስፈላጊው ነገር ባልን ወይም ሚስትን ማስደሰት ነው ብሏል ። እምነ ጋብቻ በአካል በመንፈስ በስሜትና በተግባር የሁለት ሰዎችን አንድነት የያዘ በመሆኑ እያንዳንዱ ሰው ራሱን እንደሚወደው ሚስቱን ወይም ባሏን እንደራሳቸው አድርገው መውደድ እንዳለባቸው ሲያስረዳ ነው ።

ይህ እንግዲህ የጋብቻን ትርጉም የሚገልጽ ሲሆን ክርስቲያኒቱ ሴት ግን ባካሄዷ ከሌሎች የተለየች መሆን እንዳለባት ትገመታለች ።

ስለዚህም ክርስቲያኒቱ ሴት ትእግሥትን ፣ ራስ መግታትን ፣ የሥራ ስልት ማወቅን ጥበብንና ፍቅርን ያሟላች መሆን ይኖርባታል ።

ከልጆችዋ ጋር በርህራሄና በፍቅር የምትግባባ መሆን አለባት ልጆችዋ በጠቅላላም ቤተሰቦችዋ የቤት ውስጥ ሥራ ተካፋዮች እንዲሆኑ እንደየአቅማቸው ታከፋፍላቸዋለች ። ክርስቲያን ሴት ሠርታ የምታሠራ አምና የምታሳምን እውነተኛ የቤተሰብ መምህርት ናት ።

ልጆችዋ በጠቅላላም ቤተሰቧ መጥፎውን ነገር ለመቋቋም እንዲችሉ በክርስትና እምነት እንዲመሩ ከመሠረቱ ታስጠናቸዋለች ። ይህች ሴት ተምራ የምታስተምር አዋቂና አስተዋይ መሆን አለባት በጥሩ አለት ላይ ተመስርቶ ነፋስም ሆነ ጐርፍ እንደማይጥለው ቤት ሁሉ ልጆችዋን ገና ከመሠረታቸው ማለትም ከህፃንነታቸው በሃይማኖት ትምህርት መሰርታ ስለምታሳድጋቸው ትምህርታቸው የሰፋ እውቀታቸው የዳበረ ይሆናል ።

ክርስቲያኒቱ ሴት ከእግዚአብሔር እርዳታ ጋር ሰው በእግዚአብሔር አርአያነት (ምሳሌነት) እንዲወጣ የማድረግ ችሎታ አላት ።

ይህች ሴት በያንዳንዱ እርምጃዋ እግዚአብሔር ምን ብሏል? እያለች ከልቧ በመጠየቅ ቃሉን በትጋት ታጠናለች ቤተሰቧንም ታስጠናለች ።

አንዳንድ ባሎች ከሠርግ በፊት ጥሩ ጠባይ ይኖራቸውና ካገቡ በኋላ ጠባያቸው ይለወጣል በዚህ ጊዜ ክርስቲያኒቱ ሴት ገመናዋን ለሌላ ሳታወራ ወይም በቻልተኝነትና በመናቅ ነገሩ እየቀጠለ እንዲሄድ ሳታደርግ ባለቤቷና እርሷ ለብቻቸው ሆነው ግልጽልጽ ባለ ሁኔታ እንዲወያዩ በማድረግ ፍች ከሚሉት አደጋ ትዳራቸው እንዲድን ታደርጋለች ።

በክርስቲያኒቱ ሴት በኩል መሰልቸት ፣ አለማመን ፣ ቅናት ፣ ምቀኝነት የሚባሉት ሁሉ ቦታ የላቸውም ።

ችግርና ህመም ለብዙ ትዳሮች መፍረስ ምክንያት ቢሆኑም በዚች ሴት ዘንድ ግን እነዚህ ነገሮች የበለጠ ታማኝነቷን የሚገልጹ ምስክሮች ናቸው ።

ክርስቲያኒቱ ሴት በተቻላት መጠን ከጓደኞችዋ በምንም እንዳታንስ ትጥራለች ። ነገር ግን እንደቤቷ እንጂ እንደ ጐረቤቷ ማድረግን አትፈልግም ።

ይህች ሴት ፀባየ መልካም የተመሰገነች ናት እንጂ እንደ እስስት የሚለዋወጥ ጠባይ አይኖራትም ቸር ፣ ድሆችን የምትረዳ አሳዳጊ ያጡትን ህጻናት የምታሳድግ ናት ።

ክርስቲያኒቱ ሴት እስከ መጨረሻ ድረስ ፍቅርንና ትእግስትን ርህራሄንና ይቅርታን ለባለቤቱ አሳያለሁ ። ስለ ባለቤቱ እኔው ራሴ በዓይኔ አይቼ ካላረጋገጥኩኝ በስተቀር የሚወራውን ወሬ አልሰማም ። የባለቤቴን ክፋት ለሊላ አልነግርም እንዲሁም በቃል ወይም በሥ

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል



## ጾም መጾም ከምንና ከምን ነው?

ጾም ማለት በታወቁ ዕለታት ፣ በተለዩ ሰዓታት፣ የሰው ልጅ ከምግበ ሥጋ የሚከለከልበት ወቅት ነው ። እንዲሁም ሥጋ ለነባቢት ነፍስ እንድትታዘዝ የሚያደርግ መንፈሳዊ ልጓም ነው ።ለ ማለት ይቻላል በሚገባ የማይጠበቅ እንስሳ የሰውን አዝመራና ተክል እንደሚያጠፋና እንደሚያበላሽ በጾምና በቀኖና የማይገራ ሰውነትም ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቆ ለመኖር አይችልም ።

በወርኃ ጾም መጾም የሚገባ ከሚበላ ምግብና ከሚጠጣ መጠጥ ብቻ አይደለም በጆሮ ክፉ ነገርን ከማዳመጥ ፣ በአንደበት የማይገባ ነገርን ከመናገር ፣በዓይን ክፉ ነገርን ከማየት መከልከል የጾም ሌላው አካል ነው ፤ ፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ ክፍል አንቀጽ 15 ላይ "ገንዘብ የሥጋ ግብር እንደሆነ ጾምም የነፍስ ግብር ነው " ይላል ።

በዓለመ ሥጋ ላይ የሚኖር ሰው በሚኖርበት ዘመን የሥጋ ግብርን እንዲከፍል ይጠየቃል ግብርም የሚከፍለው ከገንዘቡ ነው ግብር ሳይከፍል ግን ለመኖር አይችልም የነፍስ ግብርም ጾም እንደመሆኑ መጠን የሰው ልጅ ካልጾመ ሕያዊት ነፍሱ ከእግዚአብሔር ተለይታ የሞተች ትሆናለች ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በጥንቃቄ እንዲጾሙ ከምታዝዛቸው አጽዋማት አንዱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጾመው ዐቢይ ጾም ነው ስለዚህ ታላቅ ጾም ከመናገራችን አስቀድመን በመጀመሪያው ሳምንት ስለሚጾመው ጾም እንመለከታለን ይህ ጾም ጾመ ሕርቃል በመባል የታወቀ ነው ፣ ይህንን ጾም ማን ጾመው ? ለዚህ መረጃ የሚሆን አንድ ታሪክ እንመለከታለን ።

በኢየሩሳሌም ፎቃ ፣ በሮም ሕርቃል ነግሠው ሳሉ ፎቃ የተባለው ንጉሥ በኢየሩሳሌም በሚኖሩ ክርስቲያኖች ላይ ሥቃይና መከራ አጸናባቸው ።

ከችግራቸውም ጽናት የተነሣ እባክህ መጥተህ ከጠላቶቻችን አድነን እኛም ለአንተ እንገዛልሃለን ብለው ወደ ሕርቃል ላኩለት እርሱም ሐዋርያት በቀኖናቸው ሰው የገደለ ዕድሜ ልኩን ይጹም ብለው ሥርዓት ሠርተዋል ስለዚህ ጾምን እፈራለሁእንጂ መርዳቱንስ እረዳችሁ ነበር አላቸው ምእመናኑም እኛ እንጾምልሃለን ስላሉት መጥቶ ያንን የሚያስቃያቸውን ጠላታቸውን አጥፍቶላቸዋል እነርሱም እምስት እምስት ቀን ተከፋፍለው ጾመውለታል ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ጾም ከዓቢይ ጾም መጀመሪያ ሳምንት ይጾማል ፣ ዓቢይ ጾምን ግን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እህል ውሀ ሳይቀምስ እንደ አንድ ቀን አድርጎ ጾሞታል ፡ በጾሙም መጨረሻ ላይ ሰይጣን በሦስት ነገሮች ተፈታተነው ፡ ነገር ግን በስስት ቢመጣበት ፡ በትዕግስት ፡ በትዕቢት ቢመጣበት በትሕትና ፡ በፍቅረ ንዋይ ቢመጣበት በጸሊአ ንዋይ ድል ስላደረገው እንደ ጢስ በኖ እንደጉም ተኖ ጠፍቷል ፡ ማቴ. 4፥ 3-11

ክርስቶስ 40 ቀንና 40 ሌሊት ከጾመ በኋላ ሐዋርያትን እየመረጠ ለስብከተ ወንጌል የሚፋጠኑበትን ዘዴ አስተማራቸው ይህም የሚያጠይቀው ለመልካም ሥራ መሠረቱ ጾም መሆኑን ነው፡ ይህንንም ሊቁማር ይስሐቅ ሲገልጽ"እስመ ጾም እማ ለጸሎት ወእህታ ለአርምሞ ወጥንተ ኩሉ ገድል ሠናይ ጾም የጸሎት እናት የትእግሥት እህት የመልካም ሥራ ሁሉ መሠረት ናት"ብሏል

ሐዋርያትም ስለ ጾም በጻፉት ዲድስቅልያ በ29ኛው አንቀጽ ላይ ሲገልጹ "ዓቢይ ጾም በእናንተ ዘንድ የከበረ ይሁን" ብለዋል ክርስቲያኖች ይህንን ጾም በምንጾምበት ጊዜ ከጾሙ ጋር አብረን ልንፈጽማቸው የሚገቡ አያሌ ነገሮች አሉ በጾም ወራት ሊፈጸሙ ከሚገባቸው ትዕግሥት፣ ምጽዋት፣ ቸርነት፣ ርኅራኄ ፍቅርና የመሳሰሉትም ይገኛሉ።

ነቢዩ ኢሳይያስ ከጾም ጋር አብረው ሊፈጸሙ ስለሚገባቸው መንፈሳውያን ተግባራት ጠቅሶ ሲናገር "እኔስ የመረጥኩት ጾም ይህ አይደለምን? የበደልን እሥራት ትፈቱ ዘንድ የቀንበርንስ ጠፍር ትለቅቁ ዘንድ የተገፉትንስ አርነት ታወጡ ዘንድ ቀንበሩንስ ሁሉ ትሠብሩ ዘንድ አይደለምን ? እንጀራህንስ ለተራብ ትቆርስ ዘንድ ስደተኞችን ድሆች ወደ ቤትህ ታስገባ ዘንድ የተራቆተውንስ ብታይ ታለብሰው ዘንድ ከሥጋ ዘመድህ እንዳትሸሸግ አይደለምን? የዚያን ጊዜ ብርሃንህ እንደንጋት ይበራል ፈውስህም ፈጥኖ ይበቅላል ጽድቅህም በፊትህ ይሄዳል የእግዚአብሔር ክብር በኋላህ ሆኖ ይጠብቅሃል የዚያን ጊዜ ትጠራዋለህ እግዚአብሔርም ይሰማሃል ትጮሃለህ እርሱም እነሆ ይልሃል ይላል ትን ኢሳ.58.6-9

ጾም ከእግዚአብሔር ጋር የምታገናኝ መንፈሳዊ ድልድይ ስለሆነች በጾም ችግራቸውን አስወግደው ፍላጐታቸው የተሟላላቸው በርከት ያሉ ሰዎች ናቸው ለምሳሌ ሙሴ በጾም ሕገ እግዚአብሔርን ተቀብሏል ኢያሱ በጾም በገባዖን ፀሐይን አቁም ለነገደ እስራኤል ርስትን አካፍሏል ዳንኤል በጾም የአንበሳውን አፍ ዘግቷል ለማስረጃ ያህል እነዚህን ጠቀስኩኝ እንጂ በጾም ኃይል የተፈጸሙትን ተአምራት ሁሉ በዚህ ዓምድ ዘርዝሮ ለመግለጽ አይቻልም ።

በእግዚአብሔር ስም አምነን የምን

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# እውነተኛ ነፃነት የተጋድሎ ውጤት

ነፃነት ማለት ከጭቆና አገዛዝና ኑሮ ወጥቶ ራስን በራስ ማስተዳደር ብቸኛ ሆኖ ከመሥራት ተባብሮ መስራት በእኩልነት መኖር ለሌላው ተገዥ አለመሆን ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ስለ አርነት ወይም ስለ እውነተኛ ነፃነት ሲናገር "ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ እውነትን ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል" ብሏል ። የዮሐንስ ወንጌል ም. 8 ቁ. 31-32 ክርስቶስ ይህን ያለበት ዋና ምክንያት በዚያን ዘመን ይኖር የነበረው የአይሁድ ኅብረተሰብ ባሮማውያን አገዛዝ ሥር ወድቆ ነበር ስለዚህ ከሥጋና ከመንፈስ አርነት ወይም ነፃነት ታግሎ የሚያወጣው አጥቶ ራሱን በራሱም ቢሆን ታግሎ የባርነት ቀንበሩን መስበሩን ተስኖት፣ በድህነት በረሃብ ፣ በሥቃይ ወድቆ ግማሹም በስደት ሲንከራተት ስላየው እውነተኛ ነፃነት ያለ ተጋድሎ እንደማይገኝ ይህንን አስተማረ ።

" ኢመርሰንም በበኩሉ ስለ እውነተኛ ነፃነት ሲናገር "አውቀው ተጠንቅቀው ለማይሠሩበትና አክብረው ለማይዙት ራሱ ነፃነት ሁልጊዜ አደገኛ ነው ። ነገር ግን ካለን ነገር ሁሉ ደህናው ነገር እሱ ነው" ብሏል እንዳለውም ነፃነት ካለን ሁሉ ደህና በመሆኑ ሰዎች ሁሉ እንደ አይናቸው ብሌን ሊጠነቀቁለት ያስፈልጋል ሊጋደሉለትና እስከ መጨረሻው ሕይወታቸውን መስዋዕት አድርገው ሊያቀርቡት ይገባል ። የሰው ልጅ ኑሮው የሚሳካለት ክብሩ የሚሟላለት ከተጋድሎ ውጤት በተገኘው ነፃነት ነውና ።

በተጨማሪም ሊቁ እንዳለው አውቀውና አክብረው ነፃነት ራሱ አደገኛ ስለሚሆን መከራን ብቻ ሳይሆን ባርነትንም ያመጣል በድኅነትም ጭቆና የበይ ተመልካች ያደርጋል። ነፃነት ከሌለ በቤት ፣ በንብረት ቀርቶ በራስ ሕይወት እንኳ ማዘዝ አይቻልምና ።

በዚህ አንፃር ወደ አገራችን መለስ ብለን የታሪክን ማህደር ያየን እንደሆነ ጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን ስለ ነፃነት ያልተዋጉበት የጦር ጎራ የለም ተሰልፈውም ያልዋሉበት የጦር ሜዳ አይገኝም። ስለ ሀገራቸው ነፃነት የመከራ ውርጅብኝ ቢወርድባቸውም ከአፍ እስከ ገደፉ ሞልቶ የነበረውን የጦርነት ሞገድ ዋኝተው ተሻግረው ድል እያደረጉ ነፃነታቸውን ሲያስከብሩ ኖረዋል ።

ሮበርት ብሩት የተባለው የእስኮት ላንድ አርበኛ በተጋድሎ ውጤት ስለሚገኘው ነፃነት ሲናገር "ለክንቱ ውዳሴና ክብር ፍላጎት አይደለም ለጌትነትም ፍላጎት አይደለም የተዋጋነው ስለ ነፃነት ብቻ ነው" ብሏል። እርግጥም አርበኛ የሆኑት አባቶቻችንና እናቶቻችን በየጊዜው ከጠላት ጋር እየተዋጉ ነፃነታቸውን ሲያስከብሩ የኖሩት ውዳሴ ከንቱ ለመፈለግ የሌላውን ግዛት ለመንጠቅ ሳይሆን የድንበራቸውን አፈር ጠላት ኮቴ እንዳይረግጥና ውድ ነፃነታቸው ለዘላለም ተጠብቆ እንዲኖር በማለት ነው ።

ይህንን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጀግንነት ያልተረዳና የታሪኩን ማህደር ያልተመለከተ የፋሽስት መሪ የነበረው መሶሎኒ በሮም አደባባይ ላይ ቁሞ ከዚህ የሚከተለውን ዲስኩር ተናግሮ ነበር። "ተርባችኋል፣ ታርዛችኋል፣ ተቸግራችኋል፣ አሁንም እኔ ወደ ታደለችው ፍሬያማ ወደ ሆነችው ወደ ገነት ኢትዮጵያ ልመራችሁ ነው በዚያም ታላላቅ ከተሞችንና ለም አውራጃዎችንም ወረዳዎችን ትገዛላችሁ ፤ በዚያም ታላቅ ክብርና ለሞገስ እርጋታን ታገኛላችሁ" ብሎአል ። ይህንን በሰማን ጊዜ ነግዶ የከሰረው ሥራ ያጣው በዘንተኛ በደሞዝ ማነስ ይበሳጭ የነበረው ሠራተኛ በጠቅላላው ሴቱም ወንዱም ወዶ ዘመቻ ሆኖ ኢትዮጵያን ለመውረር በወታደርነት ይመዘግብ ጀመር ።

ቀጥሎም 1927 ዓ.ም. የፋሽስት ወታደር በምሥራቅ ኢትዮጵያ በወልወል በኩል የመጀመሪያውን ግጭት ጀመረ ። 1928 ዓ.ም. በምሥራቅም በሰሜንም ፋሽስት ሠራዊቱን አስከትቶ መሳሪያውን ሰብስቦ ለጦርነት ተዘጋጀ ።የኢትዮጵያ መንግሥት ግን በሕዝቡ በኩል እምነትና መግባባት ስላልነበረው ከመዋጋት ይልቅ ለመታረቅ ብዙ ጥሮ ነበር ሆኖም ጠላት ጦርነት እንጂ እርቅ ስላልፈለገ ሐሳቡ አልተሳካለትም ።

በዚህ ጊዜ ሦስት አስቸጋሪ ነገሮች ነበሩ እነርሱም አንደኛ በሕዝብና በመንግሥት ባለሥልጣኖች መካከል መተማመን አልነበረም ሁለተኛ በጦር አለቆችና በሠራዊቱ መካከል መግባባት የለም ሦስተኛ ቤተ ክርስቲያን የምታስገኘውን ሰፊ ጥቅም ያገኙ የነበሩት ተጠቃሚዎች ጠዋት ማታ እየተገኙ ለሚያገለግሉት ካህናት በዚያን ጊዜ አጠራር ቶፋ እየተባለ ለሚጠሩ ባመት አምስት ብር ደሞዝ ይከፈላቸው ነበር። አገልጋዮቹም በአመት አሥራ ሁለት ብር እንኳ ክፈሉን የሚል አስተያየት አቅርበው ነበር አለቆቹ ግን ከባለ ጥቅሞች ጋር ስለሚግባቡ ፍርድ ባለማግኘታቸው በቤተ ክርስቲያን ጭቅጭቅ እንጂ ሰላም አልነበረም ይህም በዚያን ዘመን የነበረው የሥጋዊውም ሆነ የመንፈሳዊው አመራር መዛባቱን ያሳያል ይሁን እ

ወደ ገጽ ፲፮ ዞሯል



# የቤተሰብ ዓምድ

አዘጋጅ ንብረት አበበ

## ቤተሰብ

አባት ፣ እናት ፣ ልጆች ዘመዶችና ሠራተኞች በአንድ ቤት ሆነው ሲኖሩ ቤተሰብ ተብለው ይጠራሉ። ከዚያ የሀገር ፣ የቀበሌ ፣ የቤተ ክርስቲያን ክንውን ብልጽግና ምንጩና ይዘቱ አሁን ከተመሠረተው ቤተሰብና ከሚከተሉት ትውልዶች ተያይዞ የሚያልፍና የሚመጣ ሆኖ የሚኖር ቤተሰብ መሆኑ ለሁላችንም እሙን ነው ።

ለዚህ ሁሉ ምክንያት የሆነው ቤተሰብ መሆኑን ካወቅን ዘንድ የሰብአዊ ዘር መርገም የሆኑት የወንጀል ሥራዎችና በሽታዎች ጠንቅ እንዳይሆኑት የቤተሰብን አካሄድና ይዘት ጠንቅቆ መጠበቅና ማስተላለፍ ቀላል ሀላፊነት አይደለም ።

እንግዲህ ቤተሰቦች የሚባሉት የተጠቀሱት ከሆኑ የእነዚህ ሁሉ ሀላፊ ወይም መሪ እንደሚታወቀው ወላጆች ናቸው ። የእነዚህን ሀላፊነትና መሪነት ሳናበላልጥ በእኩልነት ብናየው አባት ለቤተሰቦቹ የሚሆነውን ከውጪ ሲያቀርብ የእናቲቱ ሀላፊነት ደግሞ በቤት ውስጥ ይከናወናል ፣ እርግጥ ሴትየዋም ከውጭ አቅራቢ መሆንዋ አይካድም። ለቤተሰቦችዋ የሚሆነውንና ሊደረግ የሚገባውን ታውቃለች ። ትምህርት ከቤት እንዲጀምር የወደፊት ሀላፊነትንና ሙያንም ለቤቶቿ ሁሉ ታስተምራለች። ይህን የመሰሉት ሁኔታዎች እናቲቱን የቅርብ ተጠሪና አዋቂ ያደርጋታል። በዚህም ለቤተሰቦቹ ሁሉ ኑሮአቸው ትርጉም ያለውና ለወደፊትም ዓላማቸውን የሚያቅዱበትና የሚዘጋጁበት እንዲሆንላቸው ከማድረጓም በላይ ቤታቸው ከማንኛውም ቦታ የበለጠና የሚወዱት ሆኖ እንዲገኝላቸው ለማድረግ ትጥራለች። የተወዳጅነቱም ምክንያት የእናቲቱ መኖር እንደሆነ ቤተሰቦቿ ሁሉ ማንም ሳይነግራቸው ያውቃሉ።

እንዲሁም የቤተሰቡ ሁሉ ሀላፊ ዋና መሪ የሆነው አባትየው ነው የእርሱም ለቤተሰብ ያለው አገልግሎት እንደ እናቲቱ ሁሉ የቤተሰቡን አካሂድና ሁኔታ መምራትና መጠበቅ ሲሆን በሁለቱ አመራር ባለው ቤት ውስጥ የሚኖሩት ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውም እንዲሁ ለቤታቸው ለሚሆነው በመታዘዝና በመማር በቤተሰቦቻቸው ጥበቃና መሪነት ያድጋሉ። ለራሳቸው መኖር ሲጀምሩ ከኖሩበት ቤት የቤተሰብን የአኗኗር ሁኔታ ስላጠኑት በየትኛውም ቦታ ቢኖሩ አዲስ ነገር አይሆንባቸውም ።

በአንድነት ተሰባስበው በሚኖሩበት ቤት ምንም እንኳ የመጀመሪያው ሐላፊነትና እናትና አባት ላይ የተጣለ ቢሆንም ቤቱ የሁሉም ስለሆነ ለቤታቸው በአላቸው አቅም የሚያበረክቱት ድርሻ አለና የእያንዳንዳቸው ሀሳብና ዓላማ ላሉበት ኑሮአቸው ይሆናል ።

በዚህ ሁኔታ ተመሥርቶ በአንድነት የሚኖሩበት የቤተሰብ ሕይወት ከቤታቸው አልፎ ለሕብረተሰቡም የሚጠበቅበት ሀላፊነትና ድርሻ የሚሰጠውን ጥቅም ተጠሪ በሚሆኑበት ቦታ ሁሉ አርአያነቱ ከሚፈለገው በላይ ነው ለማለት ይቻላል ።

ከቤተሰብ ኑሮ የሚወሰድና ለጥቅም የሚውል የአኗኗር ሁኔታን እየተማሩ የሚኖሩ ቤተሰቦች በሚገጥማቸው የሀላፊነት ቦታ ሁሉ የሚያሳዩት የሥራ ውጤትና ከሰዎች ጋር ያላቸው የአኗኗር ሁኔታ ታላቅ ግምት ያለው ነው ።

ቤተሰቦች በአንድነት የሚኖሩበት ቤት በፍቅርና በመታዘዝ የተቀደሰ እንዲሆን ሁሉም ያስባሉ እያንዳንዳቸው ለሁሉ በመኖር ቤታቸውን ይጠብቃሉ ። የዕለታዊ ኑሮአቸው ዝግጅት ቤተሰባቸውን የሚያረካ እንዲሆን ይጥራሉ በጠቅላላው የሚኖሩበት ቤት የአስደሳች ኑሮን ትርጉም የሚገልጽ ይሆናል ።

እንግዲህ በምድር የምንመሰርተው ኑሮአችን ለሰማያዊው ኑሮ ምሳሌ እንዲሆነን ያስፈልጋል ። ለዚህም የመልካም ቤተሰብ አኗኗር ይዞታ የቱ እንደሆነ ማወቅና መምረጥ ያስፈልጋል ።በዚህ ሁኔታ የተያዘና የተጠበቀ ቤትም ከሁሉም ነገሮች የሚመረጥ ሆኖ ይገኛል በእርግጥም በዓለም ውስጥ ከሚገኙ ማንኛዎቹም ነገሮችና ቦታዎች የቤተሰባችን አቅዋም የተስተካከለ እንዲሆንልን መመኘት ብቻ ሳይሆን ማድረግ ከወደድን የቤተሰባችንን አካሄድ መጠበቅና ማስተዋል ሞራላቸውንም ማደርጀት ሀላፊነትንም አውቀው መቀበል እንዲችሉ ማድረግ የቤተሰብ ሀላፊዎች የሆኑ ሁሉ ቢያውቁ ይህ ትልቅ አስተዋይነት ነው ይህን የማይገነዘብ የቤተሰብ መሪ ለብዙ ነገሮች ተጠሪ የሆኑትን የቤተሰብ አካሎች ሊቀበለውና ሊያደርገው የሚገባው ብዙ ነገሮች እንዳይረዳና እንዲያጉድል ሊያደርገው ይችላል ።

ከዚህ ሁሉ በፊት ግን ቤተሰቡ ምን ሊያደርግ እንደሚያስፈልገው የማይጠቅመውንም እንዲተወው በዕለታዊ ተግባሮቹ ሁሉ በቀላሉ ማሳየት መልካም የኑሮ ልምድን ያጎናጽፈዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን



በወጣትነህ ወራት ፈጣሪህን አስብ (መክ. 12-1)

አዘጋጅ ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ

## የአቡነ ጴጥሮስ ሕፃናት ማሳደጊያ (ደሴ)

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ የሚመሩ የድሆች ልጆች ማሳደጊያዎች በአዲስ አበባና በየክፍለ ሀገሩ በመቋቋም ላይ ናቸው።

በዚህም መሠረት እስካሁን ድረስ በአዲስ አበባ በጎጃም ፣ በደብረ ታቦር ፣ በወረታ ፣ በወልድያ ፣ በላሊበላና በደሴ ተቋቁመው ብዙዎች የድሆች ልጆች ወደነዚህ ማሳደጊያዎች እየገቡ በመረዳት ላይ ናቸው ።

በአሁኑ የወጣቶች ዓምድ ዝግጅታችን በወሎ ክፍለ ሀገር ከተቋቋሙት ሦስት የሕፃናት ማሳደጊያዎች መካከል በተለይ በደሴ ከተማ ስለተቋቋመው የአቡነ ጴጥሮስ ሕፃናት ማሳደጊያ መጠነኛ የሆነ ማብራሪያ ለማቅረብ እንሞክራለን ።

ይህ ክፍለ ሀገር ከዚህ በፊት በከባድ ድርቅ ተመቶ የነበረ በመሆኑ ክፍለ ሀገሩን ከባድ ችግር አጋጥሞት መቆየቱ የሚታወስ ነው ። በዚህም ችግር የተነሣ በገባው በሽታና ረሀብ ምክንያት ብዙዎች ሰዎች እንደቅጠል ረግፈው ቀርተዋል፤ ከሞቱትም ሰዎች መካከል የብዙዎች ሕፃናት ወላጆች በመገኘታቸው ወላጆቻቸው የሞቱባቸው ሕፃናት እጅግ በጣም ብዙዎች እንደነበሩና ከሞት የተረፉት ሕፃናት በብርቱ ችግር ላይ በመገኘታቸው እስካሁን ድረስ መንግሥት ችግሩን ለማቃለል የድርቅ ኮሚሽን አቋቁሞ ሕዝቡን በማስተባበር የተቻለውን ያህል አገልግሎት እየሰጠ ነው ። ይሁን እንጂ ከችግሩ ክብደት የተነሣ በክፍለ ሀገሩ ውስጥ ያለው ችግር እስካሁንም ድረስ ቢሆን ፈጽሞ ተወግዷል ለማለት አንደፍርም ።

ይህንም በመመልከት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባዔ ከሌሎች ክፍላተ ሀገር ቅድሚያ ሰጥቶ በወሎ ክፍለ ሀገር ብቻ በሦስት ቦታዎች ማለት በደሴ በወልድያና በላሊበላ እነዚህን የድሆች ልጆች ማሳደጊያዎች ለማቋቋም ካስቻሉት ምክንያቶች አንዱ ይኸው ቀደም ሲል እንደተገለፀው የችግሩን መጠን በመመልከት ነው ።

በተለይ በደሴ ከተማ የሚገኘውን የአቡነ ጴጥሮስ ሕፃናት ማሳደጊያ አንድ ባንድ ተመልክተን የዚህን ሕፃናት ማሳደጊያ ሥራ መሪ ቄስ ግርማይ ተስፋ ሥላሴን አነጋግረን ሕፃናት ማሳደጊያውን በሚመለከት አንዳንድ ማብራሪያዎችን ሰጥተውናል ። በማብራሪያው መሠረት የአቡነ ጴጥሮስ ሕፃናት ማሳደጊያ የሚተዳደረው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባዔ ሥር ሲሆን ዋና ዓላማውም አሳዳጊ የሌላቸውን የሙት ልጆች በእንክብካቤ ለማሳደግና አስተምሮ ለሀገሪቱ ጤናማና አምራች ዜጋዎችን ለማበርከት ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ እነዚህን ሕፃናት ለማሳደግ ዕርዳታ የሚያገኘው "ኪንደርኖት ኀልፍ" ተብሎ ከሚጠራው በልዩ ልዩ አህጉራት በድርቅ ፣ በጦርነት ፣ በጐርፍና በበሽታ ፣ በመሳሰሉት ምክንያቶች ያላሳዳጊና ተንከባካቢ የቀሩትን ሕፃናት በመርዳት ከታወቀው ዓለም አቀፋዊና ክርስቲያናዊ በጎ አድራጎት ድርጅት ሲሆን የዚህ ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤት በምዕራብ ጀርመን በደስበርግ ከተማ ነው ።

የደሴው የአቡነ ጴጥሮስ ሕፃናት ማሳደጊያ ሥራውን የጀመረው መስከረም 1972 ዓ.ም. ሲሆን በጓድ ጌታቸው አበበ የወሎ ክፍለ ሀገር ተቀዳሚ ምክትል አስተዳዳሪ ተመርቆ የተከፈተው ሕዳር 1 ቀን 1972 ዓ.ም.ነው ። ሕፃናት ማሳደጊያው እንደተከፈተ ወደዚህ ማሳደጊያ የገቡት ሕፃናት ብዛት 80 ብቻ ነበር ። ይህም የሆነበት ምክንያት በዚያ ወቅት የነበረው ቤት አነስተኛ ስለነበረና ከ80 ሕፃናት በላይ ለመጨመር ስለማይችል ነው ። አሁን ግን የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ት/ቤት ተብሎ ይጠራ የነበረውን የወሎ ሀገረ ስብከት ለዚሁ ሕፃናት ማሳደጊያ እንዲሆን ስለሰጠ የክፍለ ሀገሩ ት/ቤቶች ጽ/ቤትም ቀደም ሲል በዚሁ ትምህርት ቤት ውስጥ ይማሩ የነበሩትን ተማሪዎች ወደ ሌሎች ት ቤቶች በመደልደል በቂ ትብብር በማድረጉ ሕፃናት ማሳደጊያው በቂና ምቹ የሆነ ቦታ ስላገኘ አሁን 100 ሕፃናትን ተቀብሎ ማደሪያ ቤት፣ ንጹሕ መኝታ ልብስና ቀለበ በአጠቃላይ መሠረታውያን የሆኑትን ነገሮች ለወጣቶቹ በማቅረብ በአዳሪነት የሚያሳድግ መሆኑን ቄስ ግርማይ ተስፋ ሥላሴ በሰጡን ማብራሪያ ለማወቅ ችለናል ።



ቄስ ግርማይ ተስፋ ሥላሴ

ሀገረ ስብከቱ ለአቡነ ጴጥሮስ የሕፃናት ማሳደጊያ የሰጠው ሕንፃ እጅግ በጣም ሰፋፊ የሆኑ 12 የመኝታ ክፍሎች ፣ 3 የሥራ ማስኪያጂያ ቢሮዎች ፣ አንድ ትልቅ የምንባብ አዳራሽና 2 ማዕድ ቤቶች ያሉት ከመሆኑም በላይ በሚገባ ለመዝናናት የሚያስችል ሰፊ ግቢ ያለው በመሆኑ ለወደፊትም ዓቅም ሲገኝ ተጨማሪ ቤት ሠርቶ ሌሎች ሕፃናትንም ለመቀበል የሚያስችል በመሆኑ እጅግ የሚያስደስት ነው ። ቄስ ግርማይ ተስፋ ሥላሴ ስለዚህ ጉዳይ ሲገልጡ ብዙ ክፍሎችን ለመሥራት የሚያስችል ብዙ ክፍት ቦታ ያለ መሆኑን ጠቁመው እርዳታ ሰጭው ድርጅት ከፈቀደ ለወደፊቱ ብዙዎች ወንዶችንና ልጃገረዶችንም ጭምር በብዛት ተቀብሎ ለማሳደግ የአቡነ ጴጥሮስ ሕፃናት ማሳደጊያ ሰፊ ዕቅድ ያለው መሆኑን አስረድተዋል ።

ወደዚሁ ሕፃናት ማሳደጊያ የሚገቡት ሕፃናት አሳዳጊ የሌላቸው የድሆች ልጆች መሆናቸው በቀበሌ ወይም በሰበካ ጉባኤ በደምብ ተመስክሮላቸው በቂ ማስረጃ ሲገኝ ነው ። አሁን በማሳደጊያው ውስጥ የሚገኙት ሕፃናት በዕድሜያቸው ዝቅተኛው ሕፃን ሰባት ዓመት ሲሆነው ከፍተኛ ዕድሜ ያለው ወጣት ደግሞ 16 ዓመት ይሆነዋል ። በአጠቃላይ በሰባትና በ16 ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ ናቸው ማለት ነው። ይህም ወደ ማሳደጊያው ሲገቡ የሚኖራቸው የዕድሜ ጣራ ነው እንጂ ከገቡ በኋላ ግን ራሳቸውን እስከሚችሉ ድረስ ከማሳደጊያው ለመውጣት እንደማይገደዱ ለመረዳት ችለናል ።

በአሁኑ ጊዜ በማሳደጊያው ውስጥ የሚገኙት ሕፃናት ዕውቀታቸውን ለማሻሻል ዘመናዊ ትምህርታቸውን የሚከታተሉት መምህራን ተቀጥረውላቸው ሳይሆን በመንግሥት ት ቤት ተመድበው ወደየምድብ ት/ቤታቸው እየሄዱ ነው ። በዚህም መሠረት በየፕሮግራማቸው ሄደው ከተማሩ በኋላ የተወሰነው ፔሬድ ሲያልቅ ወደ ሕፃናት ማሳደጊያው ተመልሰው ባላቸው ትርፍ ጊዜ ደግሞ የሃይማኖት ትምህርት እንዲከታተሉ ይደረጋል ። በዚህም መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ ፣ ቅዳሴና መዝሙር እንደሚያጠኑ ተገልጦልናል ። ሕፃናት ማሳደጊያውን ለማየት በቦታው በተገኘንበት ወቅት ሕፃናቱ መንፈሳውያን መዝሙሮችን በጥሩ ሁኔታ ሲዘምሩ ከማየታችንም በላይ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታቸውም አንዳንድ ጥያቄዎችን ጠይቀናቸው አብዛኞዎቹ ወጣቶች አጥጋቢ መልስ ስለሰጡን ተስፋ የሚጣልባቸው ሆነው አግኝተናቸዋልና ለወደፊትም በርቱ እንላቸዋለን ።

ከሥራ መሪው እንደተረዳነው ወጣቶቹ ሁልጊዜ ከምግብ በፊት ለየት ያለና ሰፋ ያለ ጊዜ የሚወስድ የጸሎት ፕሮግራም አላቸው እሁድ እሁድም ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄዱ መንፈሳዊ ፕሮግራሞችን እንዲከታተሉ ስለሚደረግ በተለይ በየቤተ ክርስቲያኑ ከሚገኙት መንፈሳውያን ወጣቶች ጋር ተሰልፈው መንፈሳዊ ትምህርትን ያጠናሉ ። ለወደፊቱ ግን በሕፃናት ማሳደጊያው ውስጥ ባለው አዳራሽ የማያቋርጥ የስብከት ፕሮግራም ለማቋቋምና ሥራውንም ለማካሄድ ዕቅድ መኖሩን ቄስ ግርማይን ጠይቀን ተረድተናል ። ስለዚህ ይህ ዕቅድ በቶሎ በሥራ ይተርጐም እንላለን ።

ወጣቶቹ ከመንግሥት ት/ቤቶች እየሄዱ ዘመናዊ ትምህርትን መማራቸው መልካም ነው ግን ቢቻል እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ የሚያስተምሩ መምህራን ተቀጥረው ዘመናዊውንና መንፈሳዊውን ትምህርት በአንድነት በተወሰነ ፕሮግራም እንዲከታተሉት ቢደረግ የበለጠ እንደሚሻል ተስፋ እናደርጋለን ።

## ክርስቲያን ሴቶች

ከገጽ ፯ የዞረ

ራ ባለቤቷን አላቃልልም ጋብቻችን የተባረከና የጸና እንዲሆን ባለኝ ኃይል ሁሉ እተጋለሁ ። ብላ የምታምን መሆን አለባት እንላለን ።

ጽሑፋችንን ለማጠቃለል ቅ መጽሐፍ ሚስትን ያገኘ መልካም በረከትን አገኘ ይላል ። ይህም ማለት ሚስት ሲል ከዚህ በላይ ከሞላ ጐደል የዘረዘርናቸውን ያሟላች ክርስቲያን ሴት ማለቱ እንጂ መቀነት ለመፍታት ከሠርጓ በፊት ከሆነ ይሆናል ካልሆነም ጥየው እወጣለሁ ብላ በልቧ ፈትታ የምታገባውን ሴት ያለመሆኑን አያጠራጥርም ።

እንግዲህ የክርስቲያኒቱ ሴት አኗኗር በእኛ አስተያየት እንዲህ መሆን አለበት ብለን ጽሑፋችንን እንደመድማለን



www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

**ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፣ ለችግራቸው መፍትሔ የሚሰጡበት ፣ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።**



**አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ**
**ስልክ ቊጥር 11-66-16**
**የፖ.ሣ.ቁ. 31-37**
**አዲስ አበባ**

ለምን እንርዳዎ አምድ አዘጋጅ

የምጠይቃችሁ እንደሚከተለው ነው። ይህውም ከዚህ በፊት አንድ "ትንሣኤ መ.ቁ. 29 የምትል መንፈሳዊ መጽሔት አግኝቼ ሳገላብጥ "ምን ልርዳዎ" የሚል ርእስ አግኝቼ ማንበቡን ተያያዝኩት አርእስቱም ከሞላ ጐደል ስለ "ሥጋ ወደሙ" የሚገልጽ ነበር ። አንድ ሰው ሥጋ ወደሙን ሲቀበል ራሱን ከሁሉ ነገር ንፁህ አድርጎ መቅረብ አለበት ይላል ። ታዲያ ይህን ባነበብኩ ጊዜ አንድ ነገር ትዝ አለኝ። ይህውም እኔ ከዚህ በፊት በልጅነቴ ቤተሰቦቼ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ እንደ መሆናቸው ሥጋወደሙን እንድቀበል ማድረጋቸው ትዝ ይለኛል ። ከዚያም አንድ ቀን እንደዚሁ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሄጄ ይመስለኛል ሥጋ ወደሙን ተቀበልኩ ። እንደዚሁ በቅርብ የክርስቶስን አዳኝነት ከመቀበሌ በፊት በቻልተኝነት በሱዳን ኢንተሪየር ሚሺን ይመስለኛል ሥጋ ወደሙን ተቀበልኩ ። እኔ የምጠይቃችሁ ከሦስቱም አብያተ ክርስቲያናት ሥጋ ወደሙን መቀበሌ ምን ነውር አለበት? ምናልባት ይቀስፈኝ ይሆን? ማድረግስ የሚገባኝ ምንድር ነው? ምንስ ለውጥ አለው? የኔ ጥያቄ ይህ ነው። ከዚህ በፊት በስልክ ጠይቄ በደብዳቤ ጻፍና በመጽሔት ይወጣልሃል ማለታችሁን አስታውሳለሁ። ኃያሉ አምላክ ሥራችሁን ይባርክላችሁ ።

ከፍያለው አበበ እድሜ 21
ፖስታ ሣ.ቁ- 50552 አ.አ

አቶ ፍያለው አበበ እርስዎ ሥጋወደሙ የተቀበሉባቸው ሦስቱ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የየራሳቸው ሥርዓት አላቸው ።በቅድሚያ ስለ ቅዱስ ቁባን ሰፊ ትምህርት ያስተምራሉ ። ማንም ሰው እምነታቸውን ሳይረዳና በመዝገባቸው ሳይመዘግብ ቅዱስ ቁርባንን አያቀብሉም ። ታዲያ እርስዎ አስቀድመው ትምህርት ተምረውና አምነው ተመዝግበው ነው? ወይስ ሳይማሩና ሳይመዘገቡ የተቀበሉት?

እየተመዘገቡ ከሆነ (ዩኒቨርሳሊስት) ዓለም አቀፍ አማኒ ወይም የዓለምን ሃይማኖት ሁሉ የሚቀበሉ መሆንዎ ነው ሳይማሩና ሳይመዘገቡ ከሆነም ማንኛውንም ነገር ሳይረዱ ተቀብለዋል ማለት ነው። ይህም የርስዎና የአብያተ ክርስቲያናቱ አለማስተዋል ይመስላል። እርስዎ ስለ ሥጋ ወደሙ እንዴት እንደሚያምኑ ብናውቅ ኖሮ ይህን ሁሉ እንዴት እንዳረጉ ለመረዳት እንችል ነበር፣ ለምሳሌ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስለ ሥጋ ወደሙ ያላት እምነት እንደዚህ ነው "ከኅብስቱና ከወይኑ ላይ ካህኑ የተመደበውን ጸሎት ቅዳሴ ከጸለየ በኋላ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ አምላክ ወይኑ ደመ አምላክ ይሆናል ይኸውም ነፍስ የተለየችው መለኮት የተዋሐደው ነው" ብላ ታምናለች ታስተምራለች ። በምታቀብልበትም ጊዜ"ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም የነሳው የአምላካችን የአማኑኤል ሥጋው ነው" እያለች ታቀብላለች ።

ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንም ምንም እንኳ ኅብስቱና ወይኑ እንደሚለወጡ ብታምንም ከላይ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክ ሳዊት ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሥጋ ወደሙ ል ዩነት መኖሩ አያጠራጥርም በ3ኛ ጊዜ የቆረቡበት የሱዳን ኢንተርየር ቤተክርስቲያንም ስለ ሥጋ ወደሙ ያላት ትምህርትና እምነት ከሁለቱም የተለያየ ነው። "ምልክት ወይም ምሳሌ" የሚል አስተሳሰብ አላት

እንግዲህ እርስዎ የትኛውን ነው? የሚያምኑ? ዋናው ጥያቄ ይህ ሆኖ ሳለ እርስዎ በሁሉም ቦታ እየተዘዋወሩ የሚቀበሉት በልማድ ይመስልናል ክርስቲያን ደግሞ በልማድ መኖር አይገባውም። ባለፈው ጊዜ ያደረጉት ሁሉ ባለማወቅ ስለሆነ ለሚመጣው በማስተዋል ይኑሩ ። የቤተክርስቲያን አባልነትዎን በአንዲት ቤተክርስቲያን ያጽኑ ይልቁንም በመጀመሪያ በተጠመቁባት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቢጸኑ መልካም ነው ። እርግጥ አንዳንድ ሰዎች እንደ እርስዎ በየቤተክርስቲያኑ ማለት የተለያየ እምነት ባላቸው አብያተ ክርስቲያን እየዞሩ ሲቆርቡ ለምን እንዲህ ታደርጋላችሁ ተብለው ሲጠየቁ "የተጣሉ ሥጋቤቶች እንጂ ሥጋው የአንድ የክርስቶስ ነው" የሚል መልስ ይሰጣሉ። ይህ ልክ አይደለም የምንቀበለው ሥጋ ወደም እውነተኛ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው በማለትና ምልክት ወይም ምሳሌ ነው በማለት መካከል ፍጹም ልዩነት አለ ይህን ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል። ከዚህም ሌላ አንድ ሳምንት ወደ አንድዋ ቤ ክርስቲያን በሌላው ሳምንት ወደሌላዋ ቤ ክርስቲያን መሄድ ከሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ውጭ ያደርጋል ምክንያቱም ከአንደኛው ዐሥራት በኩራት እንዲያወጡ ሲጠየቁ የሌላ አባል ሆነው ይገኛሉና ።



# የሃይማኖት ዐምድ

«ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፣ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. ፲፩፡፫) ።

## ምሥጢረ ንስሐ

" ንስሐ" ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ከክፋት ወደደግነት ከጥፋት ወደደህንነት ከሰይጣን ባርነት ወደ እግዚአብሔር ልጅነት ለመመለስ ያለፈውን በደል በማስታወስ የመፀፀትንና የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመቀበል የመዘጋጀትን ሁኔታ የሚገልጥ የመታደስ ምሥጢር ነው ።

የወርቅና የብር /ወዘተ/ ማእድናት ዝገት በእሳት ቀልጦ እንደሚጠራና ያረጀውም እንደሚታደስ በደል የሠራ አማኝም ወይም ከእምነት ውጭ የነበረ አረማዊ እንኳን ቢሆን አምኖ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ዝግጁ ሆኖ ከተገኘ በንስሐ ታድሶ አዲስ ፍጥረት በመሆን የእግዚአብሔርን ልጅነት ማግኘት ይችላል ። ስለዚህም ንስሐ በደለኛውን/ኃጥእ የሆነውን ሰው ምንም በደል እንዳልሠራ አድርጎ እግዚአብሔር ሲቀበለው እንደሚችል ተጽፎአል ።

ከበደል ሁሉ የከፋ አመፅ ሰው ሆኖ የማይበድል አለመኖሩ እየታወቀ ኃጢአትን በመናዘዝ የእግዚአብሔርን ምሕረት በማግኘት ፈንታ ራስን ንጹሕ አስመስሎ በማቅረብ እግዚአብሔርን ለማታለል የሚደረግ ሙከራ ነው ።

ለምሳሌ ዳዊት ከጦር አበጋዞቹ ጉልማሶች መካከል አንዱ የነበረውን የኦርዮንን ሚስት ከመቀማቱም በላይ ኦሪዮንን ከማስገደሉ የበለጠ ኃጢአት አልነበረም ነገር ግን ነቢዩ ናታን ከእግዚአብሔር ተልኮ መጥቶ ከፍተኛ በደል በመሥራቱ ሞት የሚገባው መሆኑን በልዩ ምሳሌ ገልጦ ባስረዳው ጊዜ ያለምንም መከላከያ ምክንያት ፍጹም በደል መሥራቱን አምኖ በመጸጸትና ንስሐ በመግባት የእግዚአብሔርን ምሕረት ለማግኘት በዕንባ በሐዘን የተሰበረ ትሑት ሰው ሆኖ በመገኘቱ ሀገሩን ከጥፋት ራሱን ከሞት ለማትረፍ በቅቷል ።2ሳሙ.12፣ 8-12 ።

በዚሁ አንፃር ደግሞ ሐናንያ የተባለው አዲስ አማኝ ሰጺራ ከተባለችው ሚስቱ ጋር ተሻርኮ ከገዛ ርስቱ ሽያጭ ገንዘብ ላይ ከፍሎ በመሸሸግ ለግል ጥቅሙ አውሎ በመገኘት የሠራው በደል መጠነኛ ሆኖ ሣለ ይህኑ ለጊዜው ከሰው ዓይን መሰወር ቢችልም ከእግዚአብሔር መሰወር የማይችል በመሆኑ የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ በውሸት ለመሸንገል በመሞከሩ ማለትም ተጸጽቶ ንስሐ ባለመግባቱና ዕውነቱን ለመናገር ፈቃደኛ ባለመሆኑ በቅፅበት ከነሚስቱ ለሞት አደጋ ተጋልጧል ።/የሐዋ.5.1-11

ስለዚህም ሰሎሞን በምሳሌው በደሉን በመናዘዝ ፈንታ ሰውሮ ይዞ ንፁሕ ለመምሰል የሚሞክር ሰው ከጉዳት በቀር ጥቅም የለውም ፣ በደሉን በመናዘዝ እንደገና ወደኃጢአት ላለመመለስ የሚወስን ሰው ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትን ያገኛል" ሲል የጻፈውን በማስታወስ ንስሐ በመግባት ወደ እግዚአብሔር መመለስ የአማኞች ሁሉ መንፈሳዊ ግዴታ መሆኑ መዘንጋት የለበትም ።

በመሠረቱ ገና ትምህርት ታምራት ሲጀመር የክርስቶስ ትምህርተ ወንጌል መክፈቻ (መቅድም) "የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ" የሚል እንደነበር ተጽፎአል።ምንምዓይነት በደል ይሁን ሰው አብዛኛውን ጊዜ ባለማወቅ ተሳስቶ ስለሠራው ኃጢአት ከልብ ተጸጽቶ የፈጣሪውን ምሕረት ከለመነ የደህንነት በር አይዘጋበትም ። እንዲያውም የእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት ከውቅያኖስ ባሕር ይልቅ የጠለቀበ መሆኑ በሰው ኃጢአት የሚሸነፍ አይደለም ። ስለዚህም ነበር" የሰው ልጅ ተብሎ የሚጠራው ክርስቶስ የጠፋውን ለማዳን መጥቶዋል በርሱም ያመነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ለሕማም ለሞት አሳልፎ እስከመስጠት ድረስ ዓለሙን ወዶታል " ሲል የተናገረ ።/ዮሐ.3፡16 ።ማቴ/ 18፡11-12/

ሐዋርያ ጴጥሮስም "በአረማውያን ሥርዓት በመዳራት በሥጋ ምኞት በስካር በዘፈንና ያለልክ በመጠጣት ነውር ባለበት በጣዖት አምልኮ የተመላለሳችሁበት ያለፈውን ጊዜ ይበቃል (1ጴጥ. 4፥3)

ካለ በኋላ " እንግዲህ በጊዜው ከፍ ያድርጋችሁ ዘንድ በኃያሉ እግዚአብሔር ክንድ በታች ራሳችሁንዝቅ በማድረግ እርሱ ስለናንተ ስለሚያስብ ሁሉን በርሱ ላይ ጣሉት" በማለት ምዕመናንን ወደ ንስሐ የሚጋብዝ መልእክት ሰጥቶዋል

ሐዋርያው ጳውሎስም"ስለ አንድ ዓይነት ምግብ ብኩርናውን እንደሸጠ እንደኤሳው እንዳትሆኑ ተጠንቀቁ ኤሣው በረከትን ለማግኘት በወደደ ጊዜ ተቀባይነት እንዳላገኘ ታውቃላችሁ በዕንባ ተግቶ ቢፈልገውም እንኳ ለንስሐ ስፍራ አላገኘም" በማለት ጽፎአል ፣ (ዕብ. 12፡16-17)

ይህም የሚያመለክተው ሰው ንስሐ ገብቶ ለመዳን የጊዜ ገደብ ስላለው የፀጋ ዘመን ሳያልፍበት መንፈሳዊ ጥሪን ለመቀበል ዝግጁ መሆን እንዳለበት ነው ።

እንደገናም በሮሜ. መልእክት 1፡4-5 " የእግዚአብሔር ምሕረት ወደ ንስሐ እንደሚመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የትዕግሥቱን ባለጠጋነት ትንቃለህ? ሲል ይጠይቃል ።

ክርስቶስም በወንጌል እነዚህ የገሊላ ሰዎች ይህ ስለደረሰባቸው ከሌሎቹ ገሊላውያን ሁሉ ይልቅ ኃጢአተኞች የሆኑ

ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ይህን ያውቁ ኖሮዋል ?

እጅጉ ረታ

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተጻፉት ቃሎች በእርግጥ የሚታመኑና ስሕተትና ግድፈት የማይገኝባቸው ለመሆናቸው ከሚያረጋግጡልን ማስረጃዎች አንዱ የነቢያት ትንቢት ነው ። ነቢያት ጌታ ወደፊት ሊያደርግ ያሰበውን ፈቃዱን እንዲገልጹ ከሕዝቡ መካከል መርጦ የሚያስነሳቸው ናቸው ።

የነቢያት ትንቢት የነበሩበትንና የአካባቢውን ዘመን የሚመለከት ብቻ ሳይሆን ፣ እስከ ዕለተ ምፅአት ድረስ የሚሆኑትንና ጊዜው ሲደርስ ወደፊት የሚደርሱትንና የሚፈጽሙትን ድርጊቶች ሁሉ የሚያጠቃልል ነው ። ልዑል እግዚአብሔር በወዳጆቹ በነቢያት አድሮ አስቀድሞ ሳይገልጽ ትንቢት ሳያናግር የተፈፀመ አንዳችም የታሪክ ሂደት በዓለም ላይ አይገኝም ። እዚህ ላይ ለምሳሌ ያህል ለመጥቀስ 700 ዓመት ገደማ ከልደተ ክርስቶስ በፊት የተነሳው ዳንኤል ከነበረበት ዘመን አንስቶ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ በዓለም ላይ የሚነሱትን ኃያላን መንግሥታት አነሳስና አወዳደቅ በሚያስደንቅ አኳኋን ተናግሯል። የተነገረውም ትንቢት ጊዜውን እየጠበቀ በየዘመናቱ የተፈጸመ መሆኑን ታሪክ ያረጋግጥልናል ።

በዚህ በዛሬው እትም አስቀድሞ ትንቢት ተነግሮባት ስለጠፋችው ስለጢሮስ አወዳደቅ ከታሪክ ጋር በማነጻጸር የተፈጸመውን እንደሚከተለው ለማቅረብ እንሞክራለን ።

ጢሮስ ፦ ጢሮስ በምሥራቅ ሜዲቴራንያን ባሕር ዳርቻ ላይ ያለች የፊንቂ ታላቅ የወደብ ከተማ ነች።በጥንቱ ዓለም በጦር መርከቦቿ ስመጥሩ ሀገር ነበረች፡ ነዋሪዎቿም በአካባቢው ባሉት ሀገሮች ተፈርተውና ተከብረው የሚኖሩ ነበሩ። በዚሁ በኃይሏ ከፍ ያለ ትምክሕት አድሮባት ስለነበር 590 ዓመት ከልደተ ክርስቶስ በፊት ነቢዩ ሕዝቅኤል እንዲህ ሲል ትንቢት ተናግሮባታል ። ጢሮስ ሆይ እነሆ ባንቺ ላይ ነኝ ፣ ባሕርም ሞገድዋን እንደምታወጣ እንዲሁ ብዙ አሕዛብን አወጣብሻለሁ ። የጢሮስንም ቅጥሮች ያጠፋሉ ። ግንቦቿንም ያፈርሳሉ ። ትቢያዋንም ከእርስዋ እፍቃለሁ የተራቆተ ድንጋይም አደርጋታለሁ ። በባሕር ውስጥ የመረብ ማስጫ ትሆናለች ።

...ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና ፦ የባቢሉን ንጉሥ ናቡከደነፆርን.. አመጣብሻለሁ ። ብልጥግናሽንም ይማርካሉ ሸቀጥሽንም ይበዘብዛሉ ።

...ድንጋይሽንና እንጨትሽን መሬትሽንም በባሕር ውስጥ ይጥላሉ ።....የተራቆተ ድንጋይ አደርግሻለሁ ። የመረብም ማስጫ ትሆኛለሽ ። ከእንግዲህ ወዲህ አትሰሪም ። እኔ እግዚአብሔር ተናግሬአለሁና ይላል እግዚአብሔር ። የባሕርም አለቆች ሁሉ ከዙፋኖቻቸው ይወርዳሉ መጐናፀፊያቸውን ያወጣሉ ወርቀ ዘቦ ልብሳቸውንም ያወልቃሉ መንቀጥቀጥን ለብሰው በመሬት ላይ ይቀመጣሉ ።

ነቢዩ በዚህ ትንቢቱ ጢሮስ እንደምትጠፋና ሰባት ነገሮች በትክክል እንደሚፈፀሙ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተቃኝቶ ተናግሯል ። በዝርዝር ለማስቀመጥም ፦

1. ናቡከደነፆር የጢሮስን ከተማ ይወስዳል ።
2. ትንቢቱም ይፈጸም ዘንድ ሌሎች የአሕዛብ መንግሥታት ይወርሩአታል፡
3. ከተማዪቱ የተራቆተ ድንጋይ ትሆናለች ፣
4. የመረብ ማስጫ ትሆናለች ፣
5. ድንጋዮቿ እንጨቶቿና አፈሯ በባሕር ውስጥ ይጣላሉ ፣
6. በእርስዋ መውደቅ ምክንያት ታላቅ ፍርሃት ይይዛቸዋል ፣
7. የመጀመርያዪቱ የጢሮስ ከተማ እንደገና ተመልሳ አትሠራም ።

ልክ ከዚህ በላይ በተነገረው ትንቢት መሠረት 586 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ናቡከደነፆር የባቢሎን ንጉሥ ዘምቶባት 13 ዓመት ሙሉ ከብቦ ከአስጨነቃት በኋላ በእጁ ወድቃለች ፡ ምንም እንኳ ከተማዪቱን ለመያዝ ቢችልም ነዋሪዎችዋ የከተማይቱን ያለ የሌለ ሀብት ሙልጭልጭ አርገው ጠራርገው ግማሽ ማይል ያህል ርቃ ወደምትገኘው የሜዴቴራንያን ባሕር ደሴት ሸሽተው ስለገቡ አንዳችም ነገር ሳያገኝ ወደ አገሩ ተመልሷል ። በተነገረለት ትንቢት መሠረት ግን እነሆ ከተማዪቱን ማጥፋቱ በታሪክ ተመዝግቦለታል ።

ፊንቂያውያንም በደሴቲቱ ውስጥ አዲስ የቆረቆሩዋትን የጢሮስ ከተማ ለ250 ዓመት ያህል ሳያስደፍሩ እንደተፈራች እንደተከበረች እንድትቆይ አርገዋታል ። በመጨረሻ ግን 332 ዓመት ከልደተ ክርስቶስ በፊት ታላቁ እስክንድር ፊቱን ወደ ምሥራቅ ባዞረ ጊዜ ፣ መራቂን አይተው "የጢሮስ የጦር መርከቦች ሀገሬን ይወሯት ይሆናል ፣" የሚል ግምት ስላደረበት ዘምቶባታል ።

በባሕር የተከበበችውን አዲሱቱን ጢሮስ ዘልቆ ገብቶ በቀላሉ መያዝ ባይሆንለት፣ከአሮጌይቱ ከተማ ፍርስራሽ ላይ ድንጋዩን ፣ እንጨቱን አፈሩን ሁሉ አስግዞ መሸጋገሪያ ድልድይ በባሕሩ ውስጥ አዘጋጅቶ ከተማይቱን በትንቢቱ መሠረት አጥፍቷታል ።

በጢሮስ የደረሰውንም ጥፋት የተመለከቱ ሌሎች የሜዲቴራንያን ሐገሮች ፍርሃት ረአድ ስላርበተበታቸው በራቸውን ከፍተው በሰላም እስክንድርን ስለ

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል



# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ጥንታዊትዋ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን በእንጨት ቅርጻቅርጽ ሥራ ከጥንት ጀምሮ የታወቀች ናት ። ለዚሁም ዋና አስረጅ አድርገን የምንወስደው በየቤተ ክርስቲያኑ የሚገኘው የቤተ ክርስቲያን ቅርስ ነው ።

ይኸውም በዕርፈ መስቀል የሚሰካ ትልቅ ቀዋሚ መስቀል፣ በካህናት እጅ ተይዘው የሚገኙ የእጅ መስቀሎች፣ እንዲሁም እንጨት በእንጨት ሁነው ተሠርተው የሚታጠፉና የሚዘረጉ አትሮንሶችና እነሱን የመሳሰሉት ሌሎች ቅርሳ ቅርሶች የሚሠሩት በቤተ ክርስቲያን መሆናቸው ነው ።

አሁንም ቢሆን ቤተ ክርስቲያናችን የቀድሞ ሥራዋን ሳትለውጥ እሱን በማሻሻል የእንጨት መሰንጠቂያ መጋዝ ፣ የመሳሰሉትን መሣሪያዎች አቋቁማ ሥራዋን ከቀድሞ በበለጠ ታካሄዳለች ይህንንም መሠረት በማድረግ በቤተ ክህነት ስለተቋቋመው የእንጨት ሥራ ምን ዓይነት ሥራ እንደሚሠራ የዚሁ ዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑትን መምህር ወልደ ትንሣኤን አነጋግረናቸዋል።



መምህር ወልደትንሣኤ

ትንሣኤ ይህ የእንጨት ሥራ በስንት ዓ.ም ተቋቋመ ያቋቋመውስ ማን ነው?

መምህር ወልደ ትንሣኤ ይህ የእንጨት ሥራ የተቋቋመው በየካቲት 27 ቀን 1943 ዓ.ም ሲሆን የተቋቋመው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ነው ።

ትንሣኤ ድርጅቱ ምን ምን አይነት ዕቃዎችን ይሠራል ?

መልስ ብዙ ልዩ ልዩ የሆኑትን ዕቃዎች እንሠራለን ለምሳሌ 1 መንበረ ታቦት 2/ ልዩ ልዩ ጠረጴዛዎችን 3/ ቁም ሣጥኖችን 4/ ኮሞዲኖዎችን 5/ አልጋዎችና በጠቅላላ ለቤት የሚያገለግሉ ዕቃዎችን እንሠራለን ።

ትንሣኤ የምትሠሩበት እንጨት ራሳችሁ እየገዛችሁ ነው ወይስ የሚያቀርብላችሁ ሌላ ሰው አለ?

መልስ እንጨት የሚያቀርብልን ሌላ ሰው የለም ራሳችን ነን የምንገዛው

ትንሣኤ የተሠሩትን ዕቃዎች የሚሸጥ ሌላ ሰው አለ ወይስ ራሳችሁ ናችሁ የምትሸጡት?

መልስ ማንኛውም ዕቃ በምንሠራበት ጊዜ በመጀመሪያ አንድ ግለሰብ ቀብድ ሰጥቶ ነው የሚያሠራው ቀብድ ከተቀበልን በኋላ በወደደው መልክና በወደደው ዓይነት እንሠራለታለን ሥራውንም ከጨረስን በኋላ ቀሪ ገንዘቡን እንቀበለዋለን ስለዚህ ራሳችን ነን የምንሸጠው ማለት ነው ።

ትንሣኤ ቀብድ የሚሰጥ ሰው ካላገኛችሁ ሥራ ፈትታችሁ ትቀመጣላችሁ ማለት ነው?

መልስ ሥራችን አንፈታም በቤተ ክህነት የታዘዝነውን ስንሠራ እንቆያለን እንጂ የሆነ ሁኖ ቀብድ የተቀበልናቸውም ሰዎች ጊዜ አላደርስ እያለን በብዙ ድካም ላይ ነን ያለነው እንዲያውም ቀብድ ከሰጡ በኋላ የምንመልስላቸው አሉ ።

ትንሣኤ ስንት እንደ ተሠራ ስንት እንደተሸጠ የሚቆጣጠር ሌላ ሰው አለ ወይስ ራሳችሁ ባቀረባችሁ ነው ሥራው የሚካሄደው

መልስ ራሳችን ባቀረብነው አይደለም 1ኛ የሚሠሩ ዕቃዎች በምን እንደሚሸጡ የሚተምን አለ 2ኛ ደግሞ ከተሸጠ በኋላ ገንዘቡን ገቢ መሆኑንና ገቢ አለመሆኑን የሚቆጣጠር ሌላ ሰው አለ።

ትንሣኤ ሥራው ከተቋቋመ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያስገኘው ትርፍ ምንድን ነው?

መልስ ሥራው ከተቋቋመ ማለት ከ 1943 ጀምሮ ብዙ ዘመናት ሲሠራበት እንደነበርና በመካከል በ1967 ዓ.ም. ባልታወቀ ምክንያት ቀበሌ ወስዶ ከ1967 ዓ.ም. እስከ 1971 ዓ.ም. ሐምሌ ወር ድረስ ሲጠቀምበት እንደቆየ ይታወሳል ።

ከዚህ በኋላ ግን በነሐሴ ወር 1971 ዓ.ም በመንግሥት መልካም ፈቃድ እንደገና ወደ ቤተ ክህነት ተመልሷል ።በዚህም ጊዜ ለዚህ ሥራ መንቀሳቀሻ እንዲሆን 10.000 ብር ወጭ ሁኖ ተሰጥቶ ነበር ።

ይሁን እንጂ በዚህ ዘመን ለምን እንደዋለ በምን ምክንያት እንደጠፋ ሳይታወቅ የ10.000 ብር ኪሳራ አስከትሎ ተገኘ ተባለ ። ከ1972 ዓ.ም ከመጋቢት ወር ለሥራው ማንቀሳቀሻ የሚሆን 10.000 ብር ወጭ ሆኖ እንዲሰጠኝ ስል አመለከትኩና ባመለከትኩት መሠረት በሐምሌ ወር 1972 ዓ.ም. ገንዘቡን ተረከብኩ እነሆ ሥራው በዚሁ ገንዘብ ነው ፣ የሚንቀሳቀሰው የሥራውን ማንቀሳቀሻ ከተረከብኩ ከሐምሌ 28 ቀን 72 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሕዳር 30 ቀን 1973 ዓ.ም. ድረስ ምን ያህል ገቢ እንዳስገኘ ተመርምሮ በ4 ወር ውስጥ የሥራ ማስኬጃውንና የሠራተኞቹን ደመወዝ ሸፍኖ ትርፍ 20.502 ብር ተገኝቷል ።

ለወደፊትም ቢሆን በዚህ መልክ ከሠሠራን ከዚህ የሚበልጥ ውጤት እንደምናገኝ ተስፋችን ሰፊ ነው ። ይሁን እንጂ ይህንን ውጤትም ለማግኘት የቻልነው የቤተ ክህነቱ ዋና ሥራ አስኪያ



www.ethiopianorthodox.org

ጅ አቶ መርስዔ ሐዘን አበበ በሚሰጡን የሞራል ድጋፍ በመሆኑ ሳላመሰግናቸው አላልፍም ።

ትንሣኤ በዚህ ድርጅት ውስጥ ስንት ሠራተኞች ይገኛሉ?

መልስ ከዚህ የሚሠሩት ሠራተኞች ለጊዜው 10 ብቻ ናቸው ለወደፊት ግን ሥራው በተስፋፋ መጠን ሠራተኞችም እየተጨመሩ ይሄዳሉ ማለት ነው ።

ትንሣኤ የምትሠሩባቸው መሣሪያዎች የእንጨት መሰንጠቂያ መጋዝ የመሳሰሉት ሁሉ ተገዝተው ነው ወይስ በእርዳታ የተገኙ ናቸው?

መልስ ከዚህ ቤት ውስጥ የሚታዩት የእንጨት መሣሪያዎች ሁሉ ራሳችን ገዝተን ያቋቋምናቸው ናቸው እንጂ አንድም በእርዳታ ያገኘነው ወይም የተሰጠነው የለንም ።


አንድ አውግስጢኖስ የተባለ ሊቅ ሥራ ጸሎት ነው ሲል እንደተናገረ ሁሉ ቤተ ክርስቲያናችንም ይህንን ቃል በተግባር ለመተርጐም እነሆ ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጋር በማጣመር የእንጨቱን ሥራ በመሥራት ላይ ትገኛለች። ታዲያ የዚሁ ዓይነት ሥራ በየክፍለ ሀገሩ ቢስፋፋ ትልቅ የቤተ ክርስቲያን ሥራ መሻሻል ስለሚሆን ሁሉም ተባብሮ በተቻለው መጠን ቢሠራ መልካም ነው እንላለን ።

ክንፈርግብ ማርቆስ

## እንዲህ ነው ባሕታዊ!

ከገጽ ፰ የዞረ

ለማብቀል የዘሩትንና የተክሉትን ውሃ ማጠጣትን ጣል አድርገው ቤተ ክርስቲያን እናሳንጻለን የተቸገረ እንረዳለን በማለት ከምእመናን ገንዘብ በመለመ ቢ በሚገኘው ሰፊ የልማት ቦታ ተክል እየተከሉ ዘር እየዘሩ እንዲኖሩ በ 1971 ዓ.ም ገዳማ በርከት ያሉ ባሕታውያን ተሰባስበው ነበር የሚያርሱበት በሬ ውሃ የሚያጠጡበት ሞተር ቀርቦላቸው ሳለ አትክልት ከማጠጣት ራሳቸውን በልዩ ልዩ መጠጥ ማርካትን ሰብእ ሕይወት ትምህርት ስለሚሰጣቸው ወደላሊበላና ቆቦ ብቅ ብለው ቢጐበኙ የሥራ ፍቅር ያድርባቸው ይሆና ልና ገዳማተ ላሊበላን እጅ ነሥተው የነባሕታዊ መፍቀራንና የአርጋው ላሊበላን ልማት እንዲጐበኙ ይጋበዛሉ ። ይሁን እንጂ ላሊበላን ልስም ስለም



ባሕታዊ መፍቀሬ ሰብእ የተያዩ ዛፎችን በዙሪያው ያለሙለት የችቦ መድኃኒ ዓለም ቤተ ክርስቲያን

ን እነርሱ የሚጠጡ መስል ባሕታውያን መኖራቸውን ምእመናን ሁሉ ያውቁታል ።

በዝዋይ የካህናት ማሠልጠኛ አካባ ·ሳይ ባሕታውያን የባሕታዊ መፍቀራ በመምረጥ ወደተለመደው ልመናቸው ተመልሰዋል ።

ምን አልባት እንዲህ ላሉት አስመሂድ ስንቅ ለግሱኝ በማለት የልመና ማጠናከሪያ እንዳያደርጉት ትንሣኤ ያሳስባል ።

ራደ አስረስ



## ዕውነተኛ ነፃነት …

ከገጽ ፰ የዞረ

ንጂ ይህ ሁሉ ተጽእኖ በሕዝቡ ላይ ቢፈጸምበትም አገሩንና ነፃነቱን ስለሚወድ እስከተቻለው ድረስ ከጠላት ጋር ተዋጋ ።

በመጨረሻ ግን ፋሽስት ኢጣሊያ መናኛ የሆነ ጊዜያዊ ድል አግኝቶ አዲስ አበባ ገባ በዚያን ጊዜ የነበሩት ሥጋውያንም ሆኑ መንፈሳውያን መሪዎች በየስፈራው ተበታትነው አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤል ሕዝቡ ለጠላት እንዳይገዛ አውግዘው ሲገደሉ አንዳንዶቹ ግን ከጠላት ጋር ተስማምተው ገቡ ።

ብዙኃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ስለ ሀገር ፍቅርና ስለ ነፃነት ክብር ሰፊ ገበሬው ሞፈር ቀንበሩን እየሰቀለ ፣ ሰይፉን ጎራዴውን እየታጠቀ ፣ ጠመንጃውን እያነገተ ጋሻውን እያነገበ ቄስ መስቀሉን፣ ደብተራውም መቋሚያውን፣ መነኩሴው መጽሐፍ ቅዱስን እየያዘ ሴቷም የምትነድፍበትን ዶጋንና መታረሪያ የምትፈትልበት እንዝርት እየተወች በጠቅላላው ትንሹም ትልቁም በረሃ ገብቶ ውጊያውን ቀጠለ ።

ፋሽስትም የመጣውን ሐብትና ንብረት ከማራገፍና መሣሪያውንም ከማስረከብ ጋር ጥያቄንም ጨርሶ ድል እየሆነ መመለስ ብቻ ሆነ፡፡ በመጨረሻም የሚይዘውንና የሚጨብጠውን ስላጣ በዚያን ጊዜ ሊቀ ጳጳስ የነበሩትን አቡነ ዮሐንስን ከአርበኞች ጋር እንዲያስታርቁት ጠየቀ አቡነ ዮሐንስም በነገሩ ስለተስማሙበት በአቡነ ፊሊጶስ የሚመራ አንድ የጳጳሳትን ቡድን ወደ አርበኞች ላኩ የተላኩትም ጳጳሳት ከፋሽስት ጋር ታርቀው በሰላም እንዲኖሩ አርበኞቹን ጠየቁ፡ አርበኞች ግን አንታረቅም ስላሉ ድካሙ ሁሉ መና ሆኖ ቀረ ።

." ሰሎሞን በምሳሌው ለሁሉም ጊዜ አለው ለመንቀልም ፣ ለመትከልም ጊዜ አለው ለመሸነፍም ለማሸነፍም ለድልም ጊዜ አለው፣ ለሐዘንም ለደስታም ጊዜ አለው" ሲል እንደተናገረው በእርቅም ስላልሆነለት በአርበኞች ኃይል ፋሽስት ተሸነፈ ምንምእንኳ ለአምስት ዓመት ያህል ነፃነታችን በፋሽስት ቢደፈርም በአርበኞች ኃይል በሕዝቡ መተባበር በቤተ ክርስቲያን ፀሎት በመረዳት ጊዜውም ድሉም ለኢትዮጵያ ሆነ መጋቢት 28/1933 ዓ.ም. አገር ለባላገር ስለተመለሰ የነፃነታችንና የመብታችን ባለቤቶች ለመሆን በቃን ።

እንግዲህ ነፃነት የሚገኘው በጀግኖች መስዋእትነትና በሕዝብ ሕብረት መሆኑን የተረዳን ይመስለኛል ክርስቶስ የአብርሃም ዘር ነን የሚሉትን እውነትን ብታውቁት እርነት በወጣችሁ ነበር ቢላቸው ለማንም አልተገዛንም ሲሉ መልሰዋል እኛም እንደነሱ የነፃነትን ትርጉም በመሰለን ልንተረጉመው አይገባም ።

ካልሠራንበት ነፃነት ብቻውን በቂ አይደለም እውነትንም ካልተናገርንበት ትክክለኛ ፍርድ ካልፈረድንበት ፣ በመልካም ሥራ ለወገኖች ካሀሠራንበት የነፃነት ትርጉም አልገባንም ማለት ነው የነፃነታችን ጊዜ የተባረከ እንዲሆን ሥራችን ሁሉ ስለእውነት ይሁን ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ

አዲስ አበባ

ከሁሉ አስቀድሜ በእግዚአብሔር ስም ሰላም እላችኋለሁ እግዚአብሔር በሥራችሁ ሁሉ እንዲረዳችሁ እየተመኘሁ ይህን ሀሳብ ሳቀርብ እንደምትፈጽሙት በማመን ነው ።

ወጣት ክርስቲያኖች እምነታችን አጠንክረን የሐዋርያትንና የሰማዕታትን መንገድ ተከትለን እንድንጓዝ የአንዳንድ ሰማዕታትንና ሐዋርያትን ታሪክ በተከታታይ ብታወጡት የበለጠ ትምህርት እንደሚሰጥ ይሰማኛል ይህን ለማድረግ ምን ችግር አለባችሁ ?

የመጽሔታችሁ ተከታታይ
ተማሪ ፋሲል ደርበው
መ.ሣ.ቁ.201
ጐንደር

• ተማሪ ፋሲል ደርበው ስለ ጻፍክልን አስተያየት እናመሰግናለን የሰማዕታትንና የሐዋርያትን ታሪክ የአረፉበትን ዕለት በዓላቸው የሚከበርበትን ቀንና ወር እያስመለከትን እንጽፋለን ባለፉትም ዓመታት ጽፈናል ይህንም ለማድረግ ችግር የለብንም ።



## ምሥጢረ ንስሐ

ከገጽ ፲፫ የዞረ

ይመስላችኋል ? ዕውነት እላችኋለሁ ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁም እንደነርሱ ትጠፋላችሁ" በማለት ዕቅጩን ተናግሮዋል ። (ሉቃ. 13 .3)

ስለዚህ እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ዘመን አሳልፎ አሁን በየቦታው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል ተብሎ የተጻፈውን መርሐ ግብር በመከተል የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ በማለት ቤተ ክርስቲያን ትጋብዛለች ። የሐዋ.17.30

መክብብ አጥናው

www.ethiopianorthodox.org

# ሊቃውንቶቻችን

## አባ ሮሜ ወይም አባ አብርሃም

ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አንዳንዶቹ ብሔራዊ ትምህርታቸውን በሰፊው ካጠና ቀናና የምርምር አቋማቸውን በየአቅጣጫው ካጠናከሩ በኋላ በውጭው ዓለም እየተዘዋወሩ የቋንቋ ትምህርታቸውን ለማስፋፋት ፣ የኢትዮጵያ ተወላጅ ባልሆነ የውጭ አገር ደራሲ ስለኢትዮጵያ የተጻፉትን መጻሕፍት ራሳቸው በአገር ውስጥ ተዘዋውረው በዓይን ካዩት የምርምር ሂደት ጋር ለማስተያየት ፣ የሌላውንም አገር ታሪክና ጥበባዊ ይዘት ለመመርመር ያደረጉት ድካምና ያበረከቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው

በብሔራዊና በውጭው አገር ትምህርት የተሟላ ችሎታ ያላቸውም ሊቃውንት የተጠየቁትን አሟልቶ በማስረዳት ይልቁንም ግዕዙን በመሠረቱ ከተተረጐመባቸው ከዕብራይስጥ ከዐርዕና ከዓረብ ቋንቋዎች ጋር ለማስተያየት ስለማይቸገሩ እንደነዚህ ላሉ ት ምሁራን የሚሰጠው የሊቅነት ደረጃ እጅግ በጣም ከፍ ማለት የሚገባው መሆኑን የሚገመግሙ ብዙዎች ናቸው ።

ይሁን እንጂ ይህ ዓይነቱ የሊቅነት ገጽታ እንዲያንፀባርቅ ለማድረግ የብሉይ ፣ የሐዲስ የሊቃውንት መጻሕፍት ትርጓሜና የዜማ የቅኔ ሞያ መሠረቶች መሆናቸውን ሙሉ በሙሉ ያረጋግጣሉ

ከዚህ በላይ በተገለጸው የሊቅነት መድረክ ላይ ከቆሙት አንደኛው አባ ሮሜ ፣ አባ አብርሃም ወይም አብሩካ በመባል ይጠሩ የነበሩት ኢትዮጵያዊ ናቸው ።

አባሮሜ የነበሩበት ዘመን በአሥራ ስምንተኛው መቶ ዓመተ ምሕረት መጨረሻ በአሥራ ዘጠነኛው መቶ ዓመተ ምሕረት መጀመሪያ ላይ እንደነበረ ሲታወቅ በሕገ ምንኩስና ፀንተው የኖሩ መንፈሳዊ አባት መሆናቸው ይነገርላቸዋል ። የኢትዮጵያን ጥንታዊያን ገዳማትና የታሪክና የቅርሳ ቅርስ ሥፍራዎች እየተዘዋወሩ በመጐብኘትና የረጅም ጊዜ ጥናት በመውሰድ የደከሙና በምሳሌነታቸው ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ከፍተኛ ጥቅም ያበረከቱ እንደነበሩ ይተረካል ።

በመጀመሪያ ብሔራዊውን ትምህርት ማለት የብሉያትን የሐዲሳትን የሊቃውንት መጻሕፍት ትርጓሜ የፀዋትወዜማንና የቅኔን ሙያ ካንዱ ወደሌላው በመዘዋወር በሚገባ ከተማሩና ከላይ እንደተገለጸው ምርምራቸውን በጉብኝት መልክ ጭምር ካሟሉ በኋላ ለጥቂት ጊዜ ጉባኤ ዘርግተው በማስተማር ቆይተው ትምህርት ለማስፋፋትና ቋንቋዎችን ለማጥናት ወደ ውጭ አገር ተጓዙ ።

የቅድሚያ ጉዞዋቸው ያተኰረው ወደህንድ በመሆኑ በዚሁ አገር ለሦስት ዓመታት ያህል በጣም ከታወቁትና "ጆንስ" ይባሉ ከነበሩት እንግሊዛዊ ምሁር እንግሊዝኛና ሌላም ልዩ ልዩ ቋንቋ ተምረዋል ።

በዚሁም የትምህርት ጊዜያቸው ለእንግሊዛዊ አስተማሪያቸው ስለጐንደር ጥንታዊ አመሠራረትና ታሪክ ስለጥቁር ዓባይም ዝርዝር ሁኔታ አስረድተዋል ፣ አስተማሪያቸውም መግለጫቸውን በትክክል ተከታትለውታል ።

አባ ሮሜ ጀምስ ብሩስ" የተባለውንና የታወቀውን የእስኮትላንድ ተወላጅ ከ13 ዓመታት በፊት (በዚያን ጊዜ ማለት ነው) በአገራቸው በኢትዮጵያ ጐንደር ላይ አግኝተውት ስለልዩ ልዩ የኢትዮጵያና የዓለም ታሪክ በሰፊው መነጋገራቸውን ለአስተማሪያቸው ለጆንስ በተጨማሪ አስገንዝበዋቸዋል ።

የታወቀው ደራሲ ሰርቮንትስ ዳንኩክሶት "ብርዕ የአእምሮ ምላስ ነው" ሲል እንደጻፈው ሁሉ አባ ሮሜ ያዩትን በጥያቄና በምርምር የተረዱትን ሁሉ ካንዱ ወደሌላው በሚዘዋወሩበት ወቅት ከመጻፍ ያቋረጡበት ጊዜ እንዳልነበረ ይነገራል ።

ከህንድም ወደምድረ ግብፅ ጉዞዋቸውን ቀጥለው በዋናው ከተማ በካይሮ የፈረንሣይ መንግሥት ቆንስል ከነበሩትና አሰለንዴ ቨርቢል ተብለው ይጠሩ ከነበሩት ከፍተኛ ሊቅ ተዋውቀው ለአሥራ ሁለት ዓመታት ያህል መጽሐፍ ቅዱስን በተቃና ሁኔታ ወደአማርኛ ቋንቋ ተርጉመዋል ።

ከብሔራዊና ከዓለም ሊቃውንት ጋር በመዋል እንዲሁም በትምህርት ዓለም ዕድሜያቸውን ያገባደዱት አባ ሮሜ የፈረንሳይ ፣ የግሪክንና የእንግሊዝኛ ቋንቋ አጣርተው ያውቁ እንደነበረ የታሪክ መጻሕፍት ያረጋግጣሉ ።

ከዚህም የተነሣ ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን ከሌላ ቋንቋ ወደአማርኛ መተርጐማቸው በኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ዘንድ ከፍተኛ ባለውለታ አድርጓቸዋል ፣ ከታሪክም እጅ ለእጅ አጨባብጧቸዋል ።

አባ ሮሜ ሕይወታቸውን በማይረሳ ኢ.መዋቲ ተግባር ሲያስጌጡ ከኖሩ በኋላ ከካይሮ ወደቅድስት አገር ኢየሩሳሌም ሔደው በጽኑዕ ስለታመሙ ከዚያው በሞት ተለይተው በክብር ተቀብረዋል፤

ከሞት በኋላ የታወቀው ማንነታቸው

አባ ሮሜ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ እንደኤውሮፓውያን አቆጣጠር በ1818 ዓ.ም. መጠሪያ ስሙ ቡርቫርድ በመባል የታወቀውና በግብፅ ዋና ከተማ በካይሮ የነበረው ሚሺነሪ " አባ ሮሜ" በሕይወት ሥጋ በነበሩበት ወቅት በጣም የተከበሩ በቅድስናም መልክ የሚታዩ እንደነበሩ በሰፊው አውስቷል ።

እንደኤውሮፓውያን አቆጣጠር በ1820 ዓ.ም. የእንግሊዝ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አባ ሮሜ ወደአማርኛ የተረጐሙትን መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ገዝቶ እንደኤውሮፓውያን አቆጣጠር በ1824 ዓ.ም. ወንጌል በ1829 ዓ.ም. ሐዲስ ኪዳንን ፣ በ1840 ዓ.ም. በሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን አሳተመ ።

አባ ሮሜ በዚህ ረገድ ያበረከቱትን ከፍተኛ የሥራ አስተዋጽኦ ማኅበሩ ሲያስታውሰው ይኖራል ።

የአባ ሮሜ የሕይወትና የሞት ዜና ከብዙው በጥቂቱ ከፓንክርስት ሪቻርድ ኢትዮጵያ አብዘርበር" በእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጻፈው የታሪክ መጽሐፍ በ12 ኛ ዓመት ቁጥር 2 ገጽ 140 ላይ ይገኛል፡

እነዚህን የመሳሰሉትን የትምህርት የሥራና የታሪክ ሰዎች ያስገኘችና የምታስገኝ ኢትዮጵያ ምንጊዜም ቢሆን ልትመሰገን የሚገባት ጥንታዊትና ዘመናዊት አገር ናት ።

ከአለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ



## ጾም መጾም ከምንና...

ከገጽ ፮ የዞረ

ጾመው ጾም ሁሉ ከደዌ ነፍስና ከደዌ ሥጋ ይፈውሰናል ከጠላታችን ከዲያብሎስም ያድነናል ከኃጢአትና ከበደል ነፃ ያደርገናል በጾም ወራት የበደለ መካስ የቀማ መመለስ የተጣላ መታረቅና በንስሐ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አለበት ነቢዩ ኢሳይያስ "ኑ እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይም ትነጻለች እንደደምም ብትቀላ እንደባዘቶ ትጠራለች እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ እንቢ ብትሉ ግን ብታምጹም ሰይፍ ይበላችኋል የእግዚአብሔር አፍ ይህንን ተናግሯልና" ብሏል ትን.ኢሳ.1፥18

መጾም የሚገባ ከምንና ከምን እንደ ሆነ በጾምም ወራት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን በመጠኑ ገልጸናል ስለዚህ በጾማችን በጸሎታችን ጠላታችን ሰይጣንን ድል ነሥተን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ያብቃን ።

ቄስ ልሣነወርቅ በዛብህ

## ይህን ያውቁ ኖረዋል?

ከገጽ ፲፬ የዞረ

ተቀበሉት የተነገረው ትንቢት እንደ ዚሁ ሊፈፀም ችሏል ።

ዛሬ የጥንቲቱን የጢሮስ ከተማ ለመጐብኘት የሚሄድ ሰው ቦታዪቱ ለአሣ ማጥመጃ ሥራ ምቹ በመሆኗ አያሌ የአሣ አጥማጆች መረቦቻቸውን በየቋጥኙ (በየድንጋዩ) ላይ ዘርግተው ሲያይ የተነገረው ትንቢት ተፈጽሞ ሲያገኘው ከፍ ያለ አንክሮ እንደሚይዘው አይጠረጠርም ። በመሠረቱ ጥንታዊቷ የጢሮስ ከተማ የነበረችበት ቦታ ዛሬም እንኳ ቢሆን አንድ ዘመናዊ ከተማ ሊኖረው የሚገባውን ማናቸውንም ነገር አሟልታ የምትገኝ መሆኗ ተረጋግጧል ። መቼም ለአንድ ከተማ መቆርቆር በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች መካከል ንፁሕ ውሐ ከፍተኛውን ደረጃ የያዘ ነው ። በዚችም ቦታ ላይ የሚፈልቁት አያሌ የንፁሕ ውሃ ምንጮች ቦታዪቱን ለከተማነት ሊያሳጩት ሊያበቋትም በቻሉ ነበር ። በባለ ሙያዎቹ መሐንዲሶች እንደተገመተው ከዚች ቦታ የሚፈልቀው ውሐ በቀን አስር ሚሊዮን ጋሎን እንደሚደርስ ተደርሶበታል ። ይህም ሁሉ ሆኖ እስካሁን የሊባኖስ መንግሥት መልሶ ሊሠራት ሊያቋቁማት አልቻለም ። "ከእንግዲህ ወዲህ አትሠሪም እኔ እግዚአብሔር ተናግሬአለሁና" የሚል ቃሉ ሊፈርስ አይችልምና(ይቀጥላል)



www.ethiopianorthodox.org

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች ውድድር

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች ውድድር

1. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስንት ምዕራፎች አሉ?
2. በዘመነ ኦሪት እግዚአብሔር ለሰዎች ኃጢአት ማስተሰረያ የሰጠው መንገድ ምን ነበር?
3. በዘፍጥረት ምዕራፍ 24 የሚገኘው ታሪክ የሚሰጠንን መንፈሳዊ ትምህርት በሰፊው ግለጽ ።
4. የመገናኛው ድንኳንና ኋላም የቤተ መቅደሱ መጋረጃ መንፈሳዊ ትርጉም ምን ነበር?
5. አይሁድ እንዲያከብሩ ታዘዋቸው የነበሩትን መንፈሳውያን በዓላት ከነትርጉማቸው ዘርዝር ።
6. መላእክት ለሰው ልጆች ከሰጡት አገልግሎቶች 5 ያህል ከብሉይና ከሐዲስ ጥቀስ ፣
7. እነዚህ ጥቅሶች የሚገኙበትን ጥቀስ

   1. "አፍህን ስለዲዳው ክፈት"
   2. "ተስፋየሌለው ሰው ንግግር እንደነፋስ ነው"

ተወዳዳሪዎች ሁሉ መጽሔቱ እንደደረሳችሁ በፍጥነት መልሶቻችሁን በጥንቃቄ እየሠራችሁ ላኩልን ።

መልስ ስትሰጡ መልሶች የሚገኙበትን የመጽሐፍ ስም ፣ ምዕራፍና ቁጥር ጥቀሱ ።

የጥያቄዎቹን መልሶች በሙሉ ማግኘት ባትችሉ እንኳ ሞክሩና የሠራችሁትን ላኩልን ። ተስፋ መቁረጥ የድካም ምልክት ነውና የቻላችሁትን ያህል በርትታችሁ ሥሩ ።



መልሳችሁን በሚከተለው አድራሻ ላኩ ለኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የመ.ሣ.ቁ. 1252 አዲስ አበባ ።



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org